# የአራተኛው ሻማ ምሥጢር
## እና
# ሌሎች ሁለት አጫጭር ታሪኮች

**ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው**

The Secret of the Fourth Candle

Text © 1956 Patricia St. John published by Scripture Union 207-209 Queensway, Bletchley, Milton Keynes MK2 2EB Buckinghamshire, England.

ከሚለው ነው።

አዛማጅ ትርጉም፡-
ዓለማየሁ ማሞ
ቴሌ. 56 27 86
የመ. ሣ. ቁ. 16138
አዲስ አበባ፥
ኢትዮጵያ

እርማት፡-
ናሁሠናይ አፈወርቅ
የኮምፒውተር ለቀማ፡-
መሠረት አበበ
የኅትመት ዝግጅት፡-
ፐርፌክሽን ቢዝነስ ሴንተር

Published by SIM Publishing, Box 127, A.A., ETHIOPIA

አሳታሚ፡- የኤስ. አይ. ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል፥
የፖ.ሣ.ቁ. 127፥ አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
1994 ዓ.ም (2001 A.D.)

# ማውጫ


**የታሪኩ ርእስ** ገጽ

1. አራተኛው ሻማ.......................................... 1

2. ትንሹ እንግዳ.......................................... 31

3. ኩታው.......................................... 56

Titles by Patricia M.St John
THE TANGLEWOODS' SECRET
TREASURES OF THE SNOW
STAR OF LIGHT
RAINBOW GARDEN
THE SECRET OF THE FOURTH CANDLE
THE MYSTERY OF PHEASANT COTTAGE

For older readers:
NOTHING ELSE MATTERS
THE VICTOR
I NEEDED A NEIGHBOUR

For younger readers:
THE OTHER KITTEN
FRISKA, MY FRIEND

©Patricia M. St John 1977
First published by Scripture Union 1978
The revised edition first published 2001


Scripture Union, 207-209 Queensway, Bletchley, Milton Keynes MK2 2EB

ISBN 1 85999 511X

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted, in any form, or by any means, electronic, mechanical, photocopying, recording or otherwise, without the prior permission of Scripture Union.

Printed and bound in Great Britain by Creative Print and Design (Wales) Ebbw Vale.

# አራተኛው ሻማ



# አራተኛው ሻማ

## የመጀመሪያው ሻማ

ገና ማለዳ ነው። አብነት በቤቷ በር ላይ ቆማ ብሩሁን የበጋ ቀን ትመለከታለች። አየሩ ቀዝቃዛ ቢሆንም አካባቢው ቦግ ብሏል። በሩቅ ያለው ትልቅ ፎቅ ይቅርና በመካከሉ ጉብ ያለው የመታሰቢያ ሐውልት እንኳ ጥርት ብሎ ይታያል። የምታበራው ፀሐይ ብርማ ብርሃኗን ወደ መሬት ፈንጥቃለች። ከምታየው ባሻገር እናቷ በሳምንት አራት ቀን የምትሠራበት የሃብታሞች መንደር ይገኛል።

በከተማው ዳርቻ የምትኖረው አብነት እናቷ ስለምትሠራበት የውጪ አገር ሰዎች ቤት ብዙ ጊዜ ሰምታለች። አሁንማ ቤቱ ውስጥ የኖረችበት ያህል ታውቀዋለች። ይልቁንም በዚያ ስለምትኖረው ሴት ልጅ ብዙ አድምጣለች። በየዕለቱ በምን ሰዓት እንደተነሳች፥ ቁርሷን ምን እንደበላችና ምን ዓይነት ቀሚስ እንደለበሰች ይነገራታል። ይህች ልጅ አሻንጉሊትና መጻሕፍት በሞሉበት ቤት ውስጥ እንደምትጫወት ትምህርት ቤት የምታደርሳት ሞግዚት እንዳለቻትም ሰምታለች። ይህን ሁሉ የምትነግራት የልጅቷን ክፍል የምታጸዳው እናቷ ናት። አብነትም ብትሆን ስለዚያ ቤት መስማት አይሰለቻትም።

አብነት በቤቷ ዳቦ ትጋግራለች፥ ቤት ትጠርጋለች፥ ውኃ ትቀዳለች፥ ፍየሎች ታግዳለች፥ ዱቄት ትፈጫለች፥ ልብስ ታጥባለች፥ ልጆቹንም

ትጠብቃለች። ሥራ በሌላት ጊዜ ግን በሩ ላይ ቆማ በትልቁ ቤት ስለምትኖረዋ ልጅ ማሰብ ደስ ይላታል።

«አብነት፥» አለች እናትየዋ ረጋ ባለ ድምፅ፥ «ከእኔ ጋር ሄደሽ እርዷኝ ሶፊያ ልጁን ትጠብቅ፤ ቀኑ እሁድ ነው። ብዙ እንግዶች እዚያ ቤት እንደሚመጡ ታውቂያለሽ። ለእኔ የሚተርፈኝ ሳህን አጠባ ነው። ብቻዬን ደግሞ አልችለውም። እያንዳንዳቸው በሦስት ሳህኖች ከሚበሉ ይልቅ እንደ እኛ ለምን በአንድ ሳህን አይበሉም? አይገባኝም?»

አብነት ፈጥና ዘወር አለች። ፊቷ በደስታ ተሞልቷል፤ ዐይኖቿ ያበራሉ። ወደዚያ ቤት እንድትወስዳት እናቷን ደጋግማ ለምናታለች። እርሷ ግን «የለም አይሆንም፤ እዚሁ ልጆቹን መጠበቅ አለብሽ» ነበር የምትላት፤ ዛሬ ግን ሳትጠይቅ ሕልሟ ዕውን ሊሆን ነው። ሮጣ ወደ ባሊው ሄደችና ፊትዋን ታጠበች። ከዚያም ረዥም ጥቁር ፀጉሯን አስተኛችው፤ ለዚህ ዓይነቱ ቀን ጥሩ ቀሚስ ቢኖራት ትወድ ነበር፤ ግን የላትም።

እናትየዋ ለትንሿ ሶፊያ መመሪያ መስጠት ጀመረች። «...ትንሹ ልጅ መሬት ላይ እንዳይወድቅ፤ ፍየሉ አጥሩን ጥሶ እንዳይወጣ፤ ድመቷ ወተቱን እንዳትጠጣ. . . » በዚህ ጊዜ ሁሉ አብነት እግሮቿን እያቀያየረች እንደ ዳንሰኛ ወዲያና ወዲህ ትል ነበር።

«እንሂድ እንጂ እማማ፥ ረፈደብን እኮ» አለች አብነት ቁልቁለቱን በሩጫ እየወረደች። ትንሹ ወንድሟ ብቻ መሬት አይውደቅ እንጂ ፍየሉ ወይም ድመቷ የፈለጉትን ቢያደርጉ ግድ የላትም። ወደ

ምትናፍቀው ቦታ እየሄደች ስለሆነ ስለሌላው ነገር አትጨነቅም። ከብቶች የሚግጡበትን መስክ አለፉ። በዛፎች መካከል ባለው መንገድ መገሥገሥ ጀመሩ። ወደ ከተማው በተጠጉ ቁጥር የሚሰሙት ድምፅ እየጨመረ ሄደ።

ከዚያም ወደ ትልቁ ገበያ ደረሱ፤ ግን ቀኑ እሁድ ስለሆነ ሱቆች ዝግ ናቸው። ትንሿ ልጅ የምትኖርበት ቤት ከገበያው መጨረሻ ላይ ይገኛል። ይሁንና ከፍ ያለ በመሆኑ በእብነበረድ በተሠሩ ደረጃዎች ላይ ያስወጣል። አብነት መድረሳቸውን ስታውቅ ፍርሃት ያዛት።

እናትየዋ በሩን አንኳኳች። ሌላ ሠራተኛ ከፈተ፤ አብነት ስትመኘው ወደ ነበረው ቤት ግቢ ገባች፥ ግን እንደጠበቀችው አልነበረም። ትልቅ አዳራሽ ሲሆን አንድ ፎቅ አለው። አብነት ገና አየት እንዳደረገችው ወደ ማዕድ ቤት ተጠራች፤ ከዚያም ወለሉን እንድታፀዳ ታዘዘች።

ማዕድ ቤቱ ሰፊ ስለነበር ያን ሁሉ መወልወል ቀላል አልነበረም። ያም ሆኖ አብነት አላዘነችም፤ ዛሬ ፎቁንና ወርቃማ ፀጉር ያላት ልጅ የምትኖርበትን ክፍል በሩቅ አይታዋለች። አንድ ቀን ደግሞ ላይ ወጥታ እንደምታያት ታምናለች። ሁለቱም ትናንሽ ልጃገረዶች ስለሆኑ መግባባታቸው አይቀርም።

አብነት ሳህኖቹን አጠበች፥ ድስቶቹን ፈቀፈቀች፥ የቆሸሸ ማጠራቀሚያዎቹን ደፋች። ያ የበጋ ቀን እንዲህ አለፈ። አሁን መጨለም ጀምሯል፤ የመንገዶች መብራት እየበራ ነው። አብነት

ሥራዎቿን ከጨረሰች በኋላ ማዕድ ቤት ውስጥ ቆማ ማዳመጥ ጀምራለች። እናቷ ከበስተጀርባ ያለውን ቦታ እያፀዱ ሲሆን፥ ወጥ ቤቷ ደግሞ በዕቃው ክፍል ውስጥ ተኝተዋል። አብነት ብቸኝነት ተሰማት፤ እናም ወደ ማዕድ ቤቱ በር ሮጠች፤ እዚያም ቆማ ወደ ላይ ፎቁን መመልከት ጀመረች።

ፎቁ አንድ ቢሆንም ረዥም ነው። እላይ ያለው ክፍል በሩ ክፍት ሆኖ ከውስጥ የሚመጣው ብርሃን እስከ ውጭ ይታያል። አብነት መብራቱን ስታይ ፍርሃቷ ለቀቃት፤ እናም ቶሎ ብላ ፎቁን በመውጣት ወደዚያ ክፍል ገባች።

ባለወርቃማ ፀጉሯ ልጅ ከጠረጴዛ አጠገብ ቆማ ነበር፤ አብነትን አላየቻትም። በጠረጴዛዋ ላይ የአበባ ጉንጉን ከአራት ሻማዎች ጋር ተቀምጧል። ሦስቱ ሻማዎች አልተለኮሱም። አራተኛው ግን እየበራ ነው። ይህ ለአብነት የማይረሳ ዕይታ ነበር። ለተወሰኑ ጊዜያት ድምፅ ሳታሰማ ቀጥ ብላ እንደቆመች ቆየች። ከዚያ በኋላ እናቷ ከማዕድ ቤት ሲጠሯት ሰማች። ይሄኔ ፈጥና ድምፅ ሳታሰማ ደረጃዎቹን ወረደችና በማዕድ ቤቱ መተላለፊያ ላይ ቆመች።

አብነት ወደ ፎቅ ወጥታ እንደነበር እናትየዋ አላወቁም። ይልቅስ በማዕድ ቤቱ መተላለፊያ ላይ ቆማ የነበረ መሰላቸው፤ ከዚያ ቤቱን ለቅቀው በመብራት የደመቀውን ትልቅ ገበያ አቋርጠው መጓዝ ጀመሩ። እናትየዋ ስለመሸባቸው ተናደው ስለነበር ያጉረመርሙ ነበር። አብነት ግን የምታስበው ስለበራው ሻማና ስለዚያች ልጅ ነበር።

## ሁለተኛው ሻማ

ሳምንቱ በፍጥነት አለፈ። አብነት እንደተለመደው በቤቱ ውስጥ ብዙ ሥራ ቢኖርባትም ይህ ሳምንት ግን ለእርሷ እንደ ሌሎቹ አልነበረም። ያንን ብሩህ ብርሃን የሚያመነጭ ሻማ ታስታውሰው ነበር።

እንደገና ለመሄድ ይፈቀድላት ይሆን? ይህ ጥያቄዋ ነበር። ባለፈው ልጆቹን እንድትጠብቅ የተመደበችው ሶፊያ ኃላፊነቷን በአጥጋቢ ሁኔታ አልተወጣችም። ፍየሉ ለእራት የተቀመጠውን ፍርፍር ከመብላቱም ሌላ ድመቷ የትንሹን ልጅ አፍንጫ ቧጭራው ነበር። ነገር ግን እሁድ ጠዋት ዝናብ መዝነብ ጀመረ። ይህ ከሆነ ደግሞ መተላለፊያዎቹና ወለሎቹ በተደጋጋሚ መወልወል ሊኖርባቸው ነው። የአብነት እናት ለመወሰን ቢቸገሩም በመጨረሻ ልብሳቸውን እየለበሱ እንዲህ አሉ። «አብነት ከእኔ ጋር ትሄጃለሽ፤ ወደድሽም ጠላሽ ዛሬም ልትረጂኝ ይገባል።»

«ሶፊያ ልጁን ጠብቂ፤ እንዳለፈው ጊዜ ብታደርጊ ስመለስ አሳይሻለሁ።»

ሶፊያ በመስማማት አንገቷን ካወዛወዘች በኋላ ቁርሷን መብላት ቀጠለች። እናታቸው እንዲህ ካስጠነቀቁ በኋላ ካጠፉ ልጆቻቸውን እንደሚመቱ ሶፊያ ታውቃለች።

«እሺ እማማ እረዳሻለሁ» አለች አብነት በበኩሏ። ከዚያም አብረው ቁልቁለቱን መውረድ ጀመሩ። እናም ከተማ ደርሰው የዕብነበረዱን ደረጃዎች ወጥተው ወደዚያ ቤት ገቡ። እንዳለፈው ጊዜ ሁሉ አብነት ወለሉን መወልወል ጀመረች። ወጥ ቤቱ፤

«አንድ ዕቃ ብትሰብሪ በቀላሉ አልለቅሽም» ሲሉ አስጠነቀቋት። ቀኑ ልክ እንዳለፈው እሁድ እልም ብሎ አለፈ፤ ለመመለስም ግማሽ ሰዓት ብቻ ቀራቸው። አብነት ሥራዋን የጨረሰች ስለሆነ በዚህች ጊዜ ተጠቅማ ወደምትናፍቀው ቦታ መሄድ ፈለገች።

ወጥ ቤቷ የሻይ ማቅረቢያውን ትሪ ከነብርጭቆዎቹ ይዘው ከፎቁ ወረዱ። ከዚያም ብርጭቆዎቹን እያጠቡ ሲሰጧት አብነት ደግሞ በጨርቅ ማድረቅ ጀመረች። እናቷ ወደ ጓሮ ሄደው እየሠሩ ሲሆን፥ መጨለም ጀምሯል። አብነት በጣም ደክሟታል፤ በዚህ ላይ ሻማ ስለሚበራበት የፎቁ ክፍል እያሰበች ነው።

ድንገት ብርጭቆው ከእጇ አምልጦ በሲሚንቶው ላይ ወድቆ ተሰበረባት።

ወጥ ቤቷ አንድ ጊዜ ኩርኩም አቀመሷት። ከዚያም ሊደግሟት እየተዘጋጁ፤ «አንቺ ከፉ ሚጢጢ፤ እዚህ መምጣትሽን ሴትየዋ አልሰሙም። ለዚህ የምጠይቀው እኔ ሳልሆን እናትሽ ናቸው።» አሏት።

እንደገና ሊመቷት ሲሉ አብነት አምልጣ ከማዕድ ቤቱ ወጣች። በጣም ከመደንገጧና ከመፍራቷ የተነሳ ወዴት እንደምትሄድ እንኳ አላወቀችም። የታያት ቢኖር ወደ ፎቁ መሄድና ሻማው ወደሚበራበት ክፍል መግባት ነው። ወጥ ቤቷ ለአብነት የሰነዘሩት እጃቸው ጠረጴዛውን ስለመታው ወዲያውኑ አልተከተሏትም። ጥቂት ቆይተው ቢወጡ በሩ ተከፍቷል። ስለዚህም አብነት ወደ መንገዱ የሮጠች መሰላቸውና እያጉረመረሙ ወደ ማዕድ ቤቱ ተመለሱ።

አብነት በፍጥነት ደረጃዎቹን ወጣች። በሩ ጋ ስትደርስ ያው የተለመደ ብርሃን ታያት። ወደ ክፍሉ ገብታ በሩን ወደ ኋላዋ ከዘጋች በኋላ እየተንቀጠቀጠችና እያለቀሰች በትንሿ ልጅ እግር ሥር ቁጭ አለች።

ትንሿ ሉሲ በመደነቅ አብነትን አፍጥጣ ተመለከተቻት፤ በጣም ርኅሩኅ ልጅ ስለሆነች ከእርሷ በዕድሜ የሚያንሱ ልጆች እንዲህ ሆነው ስታይ ታዝናለች። የአብነትን ችግር ልትጠይቃት ፈልጋ ነበር፤ ይሁንና ቋንቋቸው አንድ ዓይነት አልነበረም።

ሉሲ ግን አንድ ነገር አሰበች። የምትሠራውን ብታሳያት ልትጽናና ትችል ይሆናል። ስለዚህ ሄዳ የአብነትን ትከሻ በሁለት እጆቿ ያዘች። አብነት ቀና ያለችው ብዙ ቆይታ ነበር፤ ብድግ ብላ ቆመችና ዙሪያውን ማየት ጀመረች።

ጠረጴዛው፥ የአበባው ጉንጉንና አራቱ ሻማዎች በቦታቸው ነበሩ። ሁለቱ ሻማዎች ተለኩሰዋል። ሉሲ ፈገግ እያለች ለአብነት ሻማዎቹን አሳየቻት። እነዚህ ሻማዎች ሰላምን ይሰጣሉ ማለት ነው? ጸጥታው ከእነርሱ የተገኘ ይሆን?

አብነት በማዕድ ቤቱ ያጋጠማትን ችግርና መከራ ረሳችው። እርሷም ፈገግ እያለች ወደ ሉሲ ተጠጋች። የተበጫጨቀው ቆሻሻ ቀሚሷ ከሚያምረው የሉሲ ነጭ ቀሚስ ጋር ተነካካ፤ ግን ሁለቱም ይህንን ልብ አላሉትም።

ወዲያውኑ አብነት ብዙ ጥያቄዎችን ልትጠይቅ ፈለገች፤ ባለፈው ሳምንት አንድ ሻማ አሁን ደግሞ

ሁለት ለምን ተለኮሰ? ሦስተኛውና አራተኛውስ የሚለኮሱት መቼ ነው? ሁሉም ሻማዎች ሲበሩ ምን ይፈጠራል? ግን የሉሲን ቋንቋ አትችልም። ስለዚህ እንባዋ እንደገና መፍሰስ ጀመረ፤ ያልበሩትን ሻማዎች በጣቷ እያመለከተች ሉሲ እንድትለኩሳቸው ሞከረች።

ሉሲ ግን በተቃውሞ ራሷን ነቀነቀች። በዚህ አሳብ በጣም መደንገጧ ያስታውቃል። ነገር ግን አብረው መቀመጣቸው ይህን አስረሳቸው። ብዙ ሀብት ያላት ትንሿ ልዕልትና የሠራተኛዋ ልጅ የሆነችው ቆሻሻ ልጅ በጠረጴዛው አጠገብ ቁጭ አሉ። ይህ ብዙም አልቆየም። ከውጭ በመተላለፊያው ላይ የሚመጣ ሰው ኮቴ ተሰማ፤ ያ ድምፅ ከሻማው ብርሃን የሚመጣውን ሰላም ረበሸው።

አብነት ወዲያውኑ አንድ ነገር ገባት። በዚህ መገኘቷ ከችግር ነፃ አያደርጋትም። ከመጀመሪያም ቢሆን እዚህ ክፍል እንድትገባ የፈቀደላት የለም። ደግሞም የመጣችው ትንሽም ቢሆን ስሕተት ሠርታ ነው። በዚህም በጣም ደነገጠች፤ ወደ በሩ ሄደችና ቅድም በወጣችበት ፍጥነት ደረጃውን ወደ ታች መውረድ ጀመረች።

ሉሲ በዚያች ክፍል የምትውልና እህትም ሆነ ወንድም የሌላት ብቸኛ ልጅ ነበረች። ስለዚህ ብሩህ ዐይኖች ያሏት አብነት ወደ እርሷ መምጣቷ ደስ ብሏታል። ስለዚህ አብነት እንዲህ ሮጣ እንደወጣች በዚያው እንድትቀር አልፈለገችም። ሁለቱም ትንሽ ትንሽ የሚረዱት ቋንቋ እንግሊዘኛ ነው። ስለዚህ ፈጥና ወደ ውጭ ወጣችና ከፎቁ ላይ ሆና አብነትን

እንዲህ አለቻት፤ «ካም ባክ ኔክስት ሳንደይ /በሚመጣው እሁድ ተመልሰሽ ነይ/»።

ከዚያ በኋላ ሉሲ ወደ ክፍሏ ተመለሰች፤ ከውጭ የመጣችው ሞግዚቷ ነበረች። ሞግዚቷ በጥቂቱ እንግሊዝኛ መናገር የሚችሉ ጥሩ ሴት ናቸው።

አብነት ደረጃውን ስትወርድ ሞግዚቷ አላዩዋትም። ሉሲ ጋ የመጣ ሰው እንደነበረም አልገመቱም። የአብነት እናት ወደ ቤታቸው ሲሄዱ ያስቡ የነበረው ስለተሰበረው ብርጭቆ ነበር። አብነት ወደ ፎቅ ወጥታ እንደነበረ አላወቁም። ይህ በአብነትና በሉሲ መካከል የተደበቀ ምሥጢር ነበር።

አብነት ብዙ የእንግሊዝኛ ቃላትን ትርጉም ታውቃለች፤ ስለዚህም የሉሲን ድምፅ ሰምታ ትርጉሙ ገብቷታል። ሳምንቱን ሙሉ እነዚህ ቃላት እየደጋገሙ ወደ ልቧ ይመጡ ነበር «በሚመጣው እሁድ ተመልሰሽ ነይ»።

## ሦስተኛው ሻማ

ገና ሊከበር አንድ ሳምንት ብቻ ቀርቶታል። ስለሆነም በገበያው ስፍራ ያሉ ሱቆች መስታወቶቻቸውን በሚያብረቀርቁ ነገሮች አስጊጠዋል። በዚያ ምሽት ሉሲና እናቷ ሦስተኛውን ሻማ ለኮሱት።

ከዚያም ሉሲ ለእናቷ እንዲህ አለቻቸው፤ «አራተኛውን ሻማ ስናበራው አዲሱን ሱሪዬን እለብሳለሁ፥ አይደል?»

እናቷም እየሳቁ የፈለገችውን ማድረግ እንደምትችል ነገሯት። ሁልጊዜ እሁድ ማታ የሉሲ እናት አቤት አያድሩም፤ ስለዚህ ተሰናበቷት። ሉሲ ሦስቱ ሻማዎች እንደበሩ ከእናቷ ጋር ብታወራ ደስ ይላት ነበር። ስለ ገና ምሥጢር እንዲነጋገሩ ትፈልግ ነበር። ሆኖም እናቷን የሚወስደው መኪና ከውጭ ቆሟል። ሉሲ እናቷን እስከ ደረጃው ድረስ ከሸኘቻቸው በኋላ ተመለሰች። የአበባውን ጉንጉን በእጁ ይዛ ነበር።

ለነገሩ ዛሬ እናቷ ሲለዩዋት እንደሌላው ቀን አላዘነችም፥ ምክንያቱም ያቺ አብነት የምትባል ደስ የምትል ትንሽ ልጅ እንደምትመጣ ታውቃለች። ከዚያም ሞግዚቷ ለአብነት በሚገባ ቋንቋ የገናን ትርጉም የሻማዎቹንም ምሥጢር ይነግሯታል። በመጨረሻም በስጦታ ወረቀት እየተጠቀለሉ በየመሳቢያዎቹ ውስጥ የተቀመጡትን የገና ስጦታዎች ታሳያለች።

ሉሲ ሞግዚቷን ጠራችና «ዛሬ ምሽት ከእኔ ጋር እንድትሆኚ እፈልጋለሁ፤ አንድ ምሥጢር አለኝ፥ ስለዚህ ትረጂኛለሽ» ብላ ለመነቻቸው።

ሞግዚቷ ሉሲን ለመርዳት ሁልጊዜም ፈቃደኛ ነበሩ። ስለዚህ ከእሳቱ አጠገብ ቁጭ አሉ። የሚታዘዙትንም ለመስማት ይጠብቁ ጀመር። ሉሲ አንዳንድ ጊዜ ከልጆች የማይጠበቅ ትልቅ አሳብ እንደምታመነጭ ያውቃሉ።

«አንዲት ትንሽ ልጅ እኔን ልትጠይቅ ትመጣለች» አለች ሉሲ በእርግጠኝነት፤ «ግን የምትችለው

የእናንተን ቋንቋ ብቻ ነው፤ የምነግርሽን ሁሉ እንድትተረጉሚላት እፈልጋለሁ። ከዚያ በኋላ የገና ስጦታዎቼን አሳያታለሁ።»

ከባድ ጥያቄ አልነበረምና ሞግዚቷ ፈገግ በማለት ተስማሙ። ልትጠይቃት የምትመጣው የትምህርት ቤት ጓደኛዋ መሆን አለባት። እርሷም እንደ ሉሲ የሀብታም ልጅ እንደምትሆን ሞግዚቷ አልተጠራጠሩም፤ ልጅቷ የምትመጣው ከእናቷ ጋር ሊሆን ይችላል።

ግን ወዲያውኑ አንድ ነገር ሆነ። አንዲት ትንሽ ልጅ መጥታ በሩ አጠገብ ቆመች፤ ፀጉሯን በአሮጌ ሻሽ አስራለች። ዐይኗ ብሩህ ከመሆኑ በስተቀር ሰውነቷ ሁሉ ቆሽሿል። ልጅቷ አብነት ነበረች። በመጀመሪያ ሞግዚቷን አላየቻቸውም፤ የአብነት ዐይኖች ያረፉት በጠረጴዛው ላይ በሚነዱት ሦስት ሻማዎች ላይ ነበር። ይሄኔ የሞግዚቷ ፈገግታ ከፊታቸው ላይ ጠፉ፤ ተናደዱ።

«ይቻትና» አለች ሉሲ የአብነትን እጅ ጎትታ ወደ ክፍሏ እያስገባቻት። ከዚያም በሩን ወደ ኋላ ዘጋችው። አብነትንም «እንደምትመጪ አውቅ ነበር፤ ስለዚህ ሦስተኛውን ሻማ ለኩሼዋለሁ» አለቻት።

አብነት የሉሲ ንግግር አልገባትም። ነገር ግን የሉሲ አቀባበል፤ ያሳየቻትም ፍቅር ደስ አሰኛት። ስለዚህ ፊቷ በደስታ ፈካ፥ ግን ዘወር ብላ ሞግዚቷን ስትመለከት ፍርሃት ፍርሃት አላት። የሞግዚቷ ፊት ኮስተር ያለ ነበር። አብነት ፊቷን አዙራ ወደ በሩ መራመድ ጀመረች። ሉሲ ግን መንገዱን ዘጋችባትና

«ደግሞ እንዳትሮጪ፥ የሻማዎቹን ምሥጢር ልንግርሽ ነው» አለቻት። ከዚያም ሞግዚቷን «የምንግርሽን ሁሉ ለዚህች ልጅ ተርጉሚልኝ፤ እንዲገባት እፈልጋለሁ» አለቻቸው።

ሞግዚቷ በመስማማት ራሳቸውን ነቀነቁ። አብነት እሁድ እሁድ የማዕድ ቤቱን የምትወለውለው ልጅ እንደ ሆነች አውቀዋል። ይህቺ ሚጢጢ ልጅ እንዴት እዚህ መግባት እንደቻለች ገርሟቸዋል። የሉሲ እናት ነገሩን ቢሰሙ ደግሞ መናደዳቸው አይቀርም።

«እናትሽ ይህንን አይፈቅዱም» አሉ ሞግዚቷ።

«እርሷ እዚህ አታድርም» ስትል መለሰች ሉሲ፤ «ሞኝ አትሁኚ፤ ይልቅ የነገርኩሽን ፈጽሚ፤ ይቺ ትንሽ ልጅ ጓደኛዬ ናት።»

«በዓሉ ሦስት ሳምንት ሲቀረው ጀምሬ ሻማዎቹን አበራለሁ። አራተኛው ሻማ የሚለኮሰው በገና ቀን ነው። ይህ በዓል ሕፃኑ ኢየሱስ ዓለምን ከኃጢአት ለማዳን በቤተልሔም በረት መወለዱን ያስታውሰናል በያት። በሚቀጥለው ሳምንት መጥታ እንድታይ ንገሪያት፤ ምክንያቱም በዚያ ቀን አራተኛውን ሻማ እለኩሳለሁ፥ አዲሱን ሱሪ እለብሳለሁ፥ ገናም ይከበራል።»

ምግዚቷ ተስማሙ። ይህችን የማትፈለግ ልጅ ከዚህ ለማባረር ያላቸውን ምርጫ አሰቡ። ያለችውን መተርጎም አለባቸው፥ ግን የሉሲን የግብዣ ጥሪ በማጣመም ለአብነት ነገሯት።

«እንዲህ ነው የምትልሽ» አሉ ሞግዚቷ፤ «በዓሉ ሦስት ሳምንት ሲቀረው ጀምሮ ሻማዎቹን ታበራለች። ሁሉም የሚበሩት ለኢየሱስ የልደት በዓል ነው። አንቺ ግን እዚህ ምን እንደምትሠሪ አልገባኝም፤ ሁለተኛ መጥተሽ እንዳትነኪኝ፤ ያለበለዚያ ይገፔ ለወጥ ቤቷ አስረክብሻለሁ።»

አብነት ሞግዚቷን በጥርጣሬና በሃዘኔታ አየቻቸው፤ ሦስቱ ሻማዎች እየበሩ ነው። ያለው ሁኔታ ግን ደስ የሚል አይደለም። ሉሲ እንደምትፈልጋት ታውቃለች። ግን ሌላ የማይወዳት ሰው አለ፤ አሁንም ወደ ውጭ ለመሮጥ ፈለገች።

ግን ይህ ችግር የሚያመጣ አልመሰላትም። ሉሲ እንድትመጣ ትፈልጋለች፤ እርሷ ደግሞ የዚህ ክፍል ልዕልት ናት። ከዚያ ሉሲ በድንገት የአብነትን እጅ ጎትታ ወደ ክፍሉ ጥግ ወሰደቻት። በዚያም መሳቢያውን ከፍታ በስጦታ ወረቀት ተጠቅልለው የተደረደሩትን የገና ስጦታዎች አሳየቻት።

«እነዚህ ስጦታዎቼ እንደሆኑ ንገሪያት» አለች ሉሲ። «በቤታችን ላሉት ሰዎች ሁሉ ደግሞ ለአጎቶቼና ለአክስቶቼ እሰጣቸዋለሁ። እርሷም በሚቀጥለው እሁድ ከመጣች ስጦታ እንደምሰጣት ንገሪያት።»

«እነዚህ ስጦታዎቼ ናቸው ትልሻለች» አሉ ሞግዚቷ ሲያስተረጉሙ፤ «አሁን ግን ወደ ማዕድ ቤቱ ሂጂ፤ ሁለተኛ እዚህ እንዳትመጪ ትልሻለች።»

ሞግዚቷ ትርጉሙን ቢያጣምሙትም አነጋገራቸው ግን ለስለስ ያለ ነበር። አብነት የእርሳቸው አገር ሰው

ስለሆነች ሊጎዱት አልፈለጉም፥ ግን የፈሩት አንድ ነገር አለ። ይህች የተበጫጨቀ ልብስ የለበሰች ቆሻሻ ልጅ ወደ ሉሲ ክፍል እንደገባች ከታወቀ ሞግዚት ናቸውና ያስጠይቃቸዋል። አሁን የፈለጉት አብነት ከዚህ እንድትጠፋላቸው ብቻ ነው። የሚቀጥለው እሁድ አያሳስብም። ቀደም ብሎ ለወፕ ቤቷ መንገር ብቻ ነው። ወፕ ቤቷ ደግሞ እንዲህ ዓይነት ነገር ዳግመኛ እንዲፈጸም አይፈቅዱም።

አብነት በመደነቅ ስጦታዎቹን ተመለከተችና ቀና ብላ ሻማዎቹን አየች። ሞግዚቷ መኖራቸውን ረሳችው። አሁን አንድ ነገር ገብቷታል፤ ሉሲ ለምን በየሳምንቱ አንድ ሻማ እንደምትለኩስ ተረድታለች። በሚቀጥለው ሳምንት ለሚመጣው ኢየሱስ ለተባለ ሕፃን ክብር ነው። ያኔ አራቱም ሻማዎች ስለሚበሩ ክፍሉ በብርሃን ይደምቃል። ሕፃኑም እየሳቀ ወደዚህ ክፍል ይገባል። አብነት ከዚህ በፊት ስለ ኢየሱስ ሰምታ አታውቅም፥ ግን አሁን እንደገባት የተከበረ ሕፃን መሆን አለበት፤ ምክንያቱም ለእርሱ ተብሎ ሻማዎች እየተለኮሱ ነው፤ ስጦታዎችም ተዘጋጅተዋል፤ እነዚህ ሁሉ ስጦታዎች ለእርሱ እንደሚሰጡት አብነት ገመተች። በውስጣቸው የታሸገው ግን ምን ይሆን?

ለማወቅ ጓጓች። አንድን ነገር ለማወቅ እንደዚህ ጓጉታ አታውቅም። ከዚያ ዞወር ብላ ሞግዚቷን አየቻቸው፤ በክፉ ዐይን እያዩዋት ነበር። ያኔ ፍርሃቷ አገረሸ፤ ሉሲን በፈገግታ አመሰገነቻት። ከዚያ በፍጥነት እየሮጠች ደረጃዎቹን ወረደች። ነገር ግን የመጨረሻው ደረጃ ላይ ሳትደርስ በፊት የሉሲን

ድምፅ ሰማች «በሚመጣው እሁድ ተመልሰሽ ነይ» ነበር ያለቻት።

የአብነት እናት ወደ ቤታቸው ለመመለስ ቸኩለው ነበር። ግን ቶሎ መድረስ አልቻሉም። ምክንያቱም ትልቁን ገበያ ሲያቋርጡ አብነት እያንዳንዱን ሱቅ ለረዥም ጊዜ ቆማ በማየቷ ነው። ሁሉን ስታደንቅ ቆማ ስለምትቀር እናቷ እጇን ካልጎተቷት በስተቀር አትንቀሳቀስም።

አብነት በሱቆቹ በጣም የሚያምሩ ስጦታዎችን አየች፥ ሆኖም ገንዘብ ስለሌላት ልትገዛቸው አትችልም። እነዚህን ሁሉ ለሕፃኑ ኢየሱስ ብትገዛለት ደስ ይላት ነበር። ለእርሱ ስጦታን ከመስጠት ሌላ አሳብ አልነበራትም። በሚቀጥለው እሁድ አራቱ ሻማዎች ወደሚበሩበት ወደዚያ ፎቅ ትወጣለች፥ ግን ብዙ ለማቆየት አላሰበችም። የምትፈልገው እርሱን አንድ ጊዜ ብቻ ማየት ነው። ከዚያ እጁን ስማው ያመጣችለትን ስጦታ እግሩ ሥር አስቀምጣ ለመውጣት አስባለች። ምን ልትሰጠው ትችላለች? አሁን ግር ያላት ነገር ይሄ ነው።

## ስጦታው

አብነት ሳምንቱን ሙሉ የምታስበው ለኢየሱስ ስለምትሰጠው ነገር ነበር። በዚያ ሰሞን በየቀኑ ይዘንባል፤ ልጆቹ ሁሉ ብርዱን ለመሸሽ በከሰል ማንደጃው ዙሪያ ይሰበሰባሉ። ዶሮዎችና በጎች እንኳ ከዝናቡ ለመጠለል ወደ ቤቱ ጥግ ይመጣሉ። ጣሪያው ዝናብ ስለሚያንጠባጥብ ቤቱ ይበርድ ነበር። በተለይ ሕፃኑ ልጅ ያስለው ነበር። ለሁሉም ሰው

ይሄ ሳምንት አስቸጋሪ ሆኗል፥ አብነት ግን ስለ ዝናብና ብርዱ ለማሰብ ጊዜ አልነበራትም። የምታስበው አንድ ነገር ብቻ ነበር– ሕፃኑ ኢየሱስና የምትሰጠውን ስጦታ።

አንዳንድ ጊዜ ከተወዳጁ ደስተኛ ሕፃን ፊት እንደምትንበረከክ ታስባለች። ከዚያም ያዘጋጀችለትንና በሚያብረቀርቅ መሸፈኛ የተሸፈነውን ስጦታ እግሩ ሥር ታስቀምጣለች። እርሱም እጁን ወደ እርሷ ይዘረጋል። ዛሬ ደግሞ እንደተኛች በሕልሟ ሕፃኑን ስታቅፈው ዐየች። የሰውነቱ ሙቀት ለእርሷም ይሰማታል። እርሱን ስትይዘው ብቻ ብቸኝነትና ፍርሃት እንደሚለቃት ተረዳች። ሆኖም ጧት ከጣራው የሚንጠባጠበው ዝናብ ቀሰቀሳት። ይሄኔ ያየችው ነገር ሕልም እንደሆነ ገብቷታል፤ ግን ምን ልትሰጠው ትችላለች?

ምንም ነገር የላትም! በሩ ላይ ቆማ ማሰቧን ቀጠለች። ከአሳቧ የነቃችው እናቷ መጥተው ትከሻዋን በመያዝ ሲነቀንቋት ነበር።

«ቀኑን ሙሉ እዚህ ተገትረሽ ምንም አልሠራሽም» ሲሉ እናትየዋ ጮኹባትና «ምንም አትረቢም፤ ሕፃኑ ዓይንሽ እያየ እህሉን አፈሰሰው። አሁን ሂጂና ሁለት ባሊ ውኃ ቅጂልኝ፤ ደግሞ ጉድጓዱ ላይ አፍጥጠሽ እንዳትውይ» አሏት።

ከዚያ በኋላ ሂጂ ለማለት ከኋላዋ ገፈተሯት። አብነት በረዥሙ ተነፈሰችና በብርዱ እየተንቀጠቀጠች ባልዲዎቹን ይዛ ሄደች። በዚህ ቅዝቃዜ ወደ ውኃ ጉድጓድ መሄድ አስቸጋሪ ነው፥

ግን ምርጫ አልነበራትም። ስለዚህ መሮጥ ጀመረች። ቁልቁለቱን እየተንደረደረች ወረደች፣ ስትመለስ ግን መሮጥ አትችልም፣ ምክንያቱም ዳገት ነው። በዚህ ላይ ባሊዎቹ ይከብዳሉ፣ ከሁሉም በላይ ያሳዘናት ግን ለሕፃኑ የምትወስድለት ስጦታ አለማግኘቷ ነው። በዚህ ነገር በጣም አዘነች።

አጎንብሳ ዳገቱን ስትወጣ ከአንድ አሮጊት ጋር ተጋጨች። አሮጊቷ ከአብነት ጎጆ አጠገብ ነው የሚኖሩት። በዚህ ዕድሜያቸው ውኃ መቅዳት አስቸጋሪ ሆኖባቸዋል። በፊት ውኃ የሚቀዳላቸው አብሯቸው የሚኖረው የልጅ ልጃቸው ነበር፣ አሁን ግን እጁን ተሰብሯል። ስለዚህ ራሳቸው ከመቅዳት ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም። አሮጊቷ አብነት እንደገጨቻቸው በጣም ተናደዱ፣ ብዙም ሳይቆዩ አዝነው አለቀሱ። አብነት ይህን ስታይ ደንግጣ ወደ ኋላዋ ለመመለስ ፈልጋ ነበር።

አብነት በዚህ አጋጣሚ በጣም አዘነች፣ የራሷን ባልዲዎች ደልዳላ ቦታ ላይ አኖረች። ከዚያም የአሮጊቷን ባሊ ተቀበለቻቸውና «ውኃውን እኔ እቀዳልዎታለሁ፣ ወደ ቤትዎ ተመለሱ» አለቻቸው። እናም ወደ ውኃው ጉድጓድ ተመለሰች፣ አሮጊቷም በመደነቅ ተሞልተው ወደ ቤታቸው ሄዱ። አብነት ባሊውን በውኃ ሞልታ ስትመለስ አሮጊቷ ከአልጋቸው ሥር ዕቃ እየፈለጉ ነበር። አብነትም ባሊውን በሩ ላይ አስቀምጣ ለመመለስ ዘወር አለች። ነገር ግን አሮጊቷ ወዲያውኑ ተነስተው ደረሱባት፣ እንዲህም አሏት፣ «ጥሩ ልጅ ነሽ፣ ስለዚህ አሁን ከጠበስኳቸው ብስኩቶች አንዱን እሰጥሻለሁ» ይህን

እያሉ አንድ ለስላሳ ዳቦ መሳይ ነገር በእጇ ላይ አኖሩላት።

አብነት በደስታ ተሞላች፤ ያገኘችውን ስጦታ እያየች በዝናቡ ላይ ቆመች፥ ምክንያቱም ሕፃናት ብስኩት በጣም ይወዳሉ። ይህኛው ብስኩት ጠፍጣፋ ሲሆን እንደ ስፖንጅ እንዲነፋ ታስቦ በዘይት መጥበሻ ላይ የተጋገረ ነው።

አብነት በጣም ደስ ስላላት ብስኩቱን ይዛ ወደ ቤቷ ሮጠች፤ ግን አጥሩ ጋ ስትደርስ የራሷ ባልዲዎች ትዝ አሏት። ስለዚህም ልታመጣቸው ሄደች፤ እናቷ ግን አላዩዋትም ነበር። ውኃውን ይዛ ከመጣች በኋላ ዝም አለች፤ ምሥጢሯን ለማንም አልነገረችም።

ስጦታውን ለመጠቅለል እንደ ሉሲ ዓይነት ብልጭልጭ ወረቀት የላትም፥ ግን ሁለት ትልልቅ ቅጠሎች ወስዳ ብስኩቱን ከመሃል አስቀመጠችው። ከዚያ ወደ ጥግ ወስዳ ከአጎዛው ሥር ከሸሸገችው በኋላ መሸት ሲል ወደ መኝታ ቦታዋ ይዛው ሄደች።

ቀኑ ደረሰ። አብነትም ከእናቷ ጋር ወደ ከተማ ለመሄድ ተነሳች፤ ግን ስጦታውን እናቷ እንዳያዩባት ማድረግ አስቸጋሪ ስለነበር ራሷ ላይ አስቀምጣ በላዩ ላይ የአንገት ልብስ ተከናነበች። እንዳይወድቅም ቀጥ ብላ መራመድ ጀመረች። ትልቁ ቤት ስትደርስ አንገቷን አሟት ነበር። ስጦታውን በአንገት ልብሷ ጠቅልላ ከማዕድ ቤቱ ጥግ አስቀመጠችው። እንግዲህ ቀኑን ሙሉ መሥራት አለባት። ኋላ ጨለምለም ብሎ የመንገድ መብራቶች ሲበሩ ወደ ፎቁ መሮጥ

ትችላለች። እዚያ አራቱ ሻማዎች ሲበሩ ማየትና ያዘጋጀችውን ስጦታም ለሕፃኑ መስጠት ትችላለች።

ሕፃኑ መጥቶ እንደሆነ ለማወቅ አብነት ጓጓች፤ አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ደረጃውን እየወጣች መተላለፊያው ላይ በመቆም አዳመጠች፥ ሆኖም የሚጫወትና የሚስቅ ሕፃን ድምፅ አልሰማችም። አካባቢው ጸጥ ብሏል። የሉሲ ክፍል ተዘግቷል፤ ግን ይሄ ብዙም አላስጨነቃትም። ምናልባት ሕፃኑ የሚመጣው በአውሮፕላን ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ቤተሰቡ ሁሉ እርሱን ለመቀበል ሄደው ይሆናል።

የአብነት እናት እንደተለመደው ሥራ በዝቶባቸዋል፤ ወጥ ቤቷ ግን በአካባቢው የሉም። አብነት ብቻዋን ነበረችና ወደ ፎቁ ለመውጣት ሰዓቱ አሁን እንደሆነ ገመተች። አራተኛው ሻማ የሚበራበት ሰዓት አሁን ሊሆን ይችላል። ተስፋ፥ ፍቅር፥ ፍርሃት፥ ብርታት፥ መደነቅና ጉጉት ተፈራረቁባት። ስጦታ የጠቀለለችበትን ቆሻሻውን ሻርፕዋን ጥብቅ አድርጋ ይዛ ወደ ጨለማው መተላለፊያ ሮጠች።

ደረጃውን ተጠግታ ወደ መጨረሻው ተመለከተች፤ በሩ ተከፍቷል። ብርሃኑም ካለፉት ጊዜያት የበለጠ ደምቋል፤ ምክንያቱም ነገ ገና ስለሆነ ሉሲ አራቱንም ሻማዎች ለኩሳለች።

ቤቱ ጸጥ ብሏል፤ ምናልባት ሕፃኑ ተኝቶ ይሆናል። አብነት በጣም ደስ እያላት ደረጃውን ወጣች፤ ወደ በሩም ተራመደች። ነገር ግን ገና ደረጃውን ጨርሳ ራመድ እንዳለች አንድ ሰው በእጁ ያዛት። ወደ

ታችም ይዟት ይወርድ ጀመር፤ የሚጎትታት ማን እንደሆነ ከማወቋ በፊት አብነት ታች ወረደች። ማዕድ ቤቱ ጋ ሲደርሱ እዚያ መብራት ስለነበረ ማን እንደያዛት ተረዳች። ወጥ ቤቷ ናቸው!

«አውቄያለሁ» አሉ ወጥ ቤቷ በጥፊ እየመቷት፤ «ሞግዚቷ ነግራኛለች፤ ወደ ፎቁ እንደምትወጪ ሰምቼአለሁ፤ ሁለተኛ እንዳይለመድሽ፤ ያለበለዚያ ከጎንሽ ታገኚዋለሽ፤ ለእናትሽም እነግራታለሁ።»

አብነት ጮኸች፤ ወጥ ቤቷም አፍዋን በእጃቸው አፍነው ድምጽዋ እንዳይሰማ አደረጉ። ከዚያ ወደ ዋናው በር እየገፈተሩ ወስደው ከኋላ ዘጉባት። አብነት መውጫው ላይ ብቻዋን ቆመች፤ ስጦታውን አሁንም በእጇ እንደያዘችው ነው።

ወዴት መሄድ እንዳለባት አላወቀችም። ብቻ ከዚህች ክፉ ወጥ ቤት መራቅ አለባት። ስለዚህ ሰው ወደ በዛበትና በመብራት ወደ ደመቀው ትልቁ ገበያ ሮጠች፥ ግን ምንም አላየችም፤ እያለቀሰችም ነበር። ያሳዘናት በጥፊ መመታቷ ወይም ወደ ታች መጎተቷ አይደለም፤ እርግጥ ይህ ጎድቷታል። በጣም ቅር ያላት ግን ሕፃኑን አለማየቷ ነው። ልታገኘው ጥቂት ነበር የቀራት፤ በጣም ተጠግታ ነበር። ሕፃኑ እዚያ ቤት እንዳለ አልተጠራጠረችም። ይሄኔ የአራቱን ሻማዎች ብርሃን እያየ እንቅልፍ ወስዶት ይሆናል። ግን አልጋው ሥር ሊቀመጥለት የሚገባ ስጦታ አለ። ያ ደግሞ አሁንም አብነት እጅ ላይ ያለው ብስኩት ነው።

ይህን እያሰበች ጉዞዋን ቀጠለች። መንገዱን ስታቋርጥ ደግሞ ብዙ ሰዎች ተንጫጩ፤ ትራፊኩም ፊሽካ ነፋ፤ ከዚያም መኪና በድንገት ፍሬን ሲያዝ የሚሰማው ሲጢጢጢጢጥ የሚል ድምፅ ተሰማት። ለካስ ሳታውቀው መኪና መንገድ ውስጥ ገብታ ኖሮ አብነትን መኪና ገጫት። ስለዚህ አስፋልቱ ላይ ተዘረረች፤ ብዙ ሰዎች ከበቧት፥ በመጨረሻ ግን አንድ አንቡላንስ እየበረረ መጥቶ ወደ ሆስፒታል ወሰዳት።

## ሕፃኑ

አብነት እስከሚቀጥለው ቀን የት እንዳለች አላወቀችም። ተገጭታ ስትወድቅ አስፋልቱ ጭንቅላቷን መትቷት ነበር። ጎማው ስለሄደባት አንዱን እግሯን ሰብሯታል። ከሰዓት በኋላ ራሷን አወቀች፤ ያን ጊዜ የመዝሙር ድምፅ የሰማች፥ ከርቀትም የሻማ ብርሃን ያየች መሰላት፤ ግን ‹በሕልሜ መሆን አለበት› ብላ አሰበች።

ነገር ግን አመሻሹ ላይ ሙሉ በሙሉ ስትነቃ በሕልሟ እንዳልሆነ ተረዳች። የእግሯ ሕመም ተሰማት፤ ራሷም ያዞራት ነበር። የት እንዳለች አልገባትም። ስለዚህ ጸጥ ብላ ተኝታ ዙሪያዋን ማየትና ማዳመጥ ጀመረች። ከፍ ያለ አልጋ ላይ መተኛቷ አስፈራት፤ ምክንያቱም እርሷ የለመደችው መሬት ላይ መተኛት ነው። ግን በግራም ይሁን በቀኝ ብዙ ሰዎች አልጋ ላይ ተኝተዋል። ሁሉም የተረጋጉ ስለሆነ ቦታው ሰላማዊ እንደሆነ ገባት። በቤቱ አንድ ጥግ ከጥድ ዛፍ ተሠርቶ በመብራት

ያጌጠ የገና ዛፍ እያዩ የቆሙ ሰዎች ይታያሉ። በዙሪያውም በርካታ ሻማዎች ይበራሉ። በዛፉ ዙሪያ አዳዲስ ልብስ የለበሱ ሕፃናት ክብ ሠርተው ተቀምጠዋል። ደግሞም እንዲህ እያሉ ይዘምራሉ፡—

ሕፃኑ ኢየሱስ
ጋደም የሚልበት፥
ከግርግም በስተቀር
ከከብቶቹ በረት፥
አልተገኘም ቦታ
ለትንሹ ጌታ።

የአብነት ልብ በደስታ ዘለለ። «ትንሹ ጌታ ኢየሱስ» እነ ሉሲ ቤት ይመጣል ተብሎ የነበረው ሕፃን መጠሪያ ነው። ግን እዚያ ከመሄድ ይልቅ እዚህ የመጣ ይመስላል። ልጆቹ ስለ እርሱ እየዘመሩ ነው። ደግሞ ለእርሱ ክብር ሲባል አራት ሳይሆን ከአምሳ የሚበልጡ ሻማዎች ተለኩሰዋል።

አብነት እንደገና እንቅልፍ ወሰዳት፤ ስትነቃ ግን መሽቶ ነበር። ሻማዎቹ የሉም። የሚዘምሩ ልጆችም አልነበሩም፤ ጥግ ላይ ብቻ አንድ ደብዛዛ መብራት አለ። የሚሰማው የበሽተኞች ማንኮራፋት ነው። አብነት ከትራሷ ቀና ብላ ዙሪያዋን መመልከት ጀመረች። የምሽቱ ተረኛ ነርስ ስላየቻት ወደ እርሷ መጣች። ተሽሏት እንደሆነም ጠየቀቻት፤ አብነት የነርሷን እጅ ሳመች።

አብነት ነርሶች ደስ ይሏታል። ከአንድ ዓመት በፊት ትንሹ ወንድሟ በጋለ የከሰል ምድጃ ላይ

በመቀመጡ የመቃጠል አደጋ ደርሶበት ነበር። አብነት ቁስሉን ለማሳከም ጠዋት ጠዋት ወደዚሁ ሆስፒታል ታመላልሰው ነበር። የምታከመው ነርስ ሁሌም ርኅሩኅና ደስተኛ ነበረች። እንዲያውም ሕፃኑ ካለቀሰ ከረሜላ በመስጠት ዝም ታስኘው ነበር። ነርሶች ሁሌም የፍቅር ሰዎች ናቸው። በእነርሱ መተማመን ይቻላል!

«ሕፃኑን ላየው እፈልጋለሁ» አለቻት አብነት ነርሷን። በመቀጠልም «የት ነው ያለው ወደ መኝታው ሄደ እንዴ?» ብላ ጠየቀቻት።

«የትኛው ሕፃን?» አለች ነርሷ ረጋ ብላ፥ «ሕፃኑ ስትይ ወንድምሽን ማለትሽ ነው?»

«አይደለም» አለች አብነት። ቀጠል አድርጋም «ኢየሱስ የተባለው ሕፃን ነው። እነ ሉሲ ቤት ይመጣል ተብሎ ነበር፤ እርሱ ግን እዚያ መሄዱን ትቶ እዚህ መጣ። ሕፃናት ስለ እርሱ ዘመሩ፥ ሻማዎችም ተለኮሱ። አሁን የት አለ? ስጦታ አዘጋጅቼለት ነበር፥ አሁን ግን ዕቃው የት እንዳለ አላውቅም።»

ነርሷ ነገሩ ግራ ገባት። ይህች ገና ያልሠለጠነች ትንሽ ልጅ እንዴት ስለ ሕፃኑ ኢየሱስ ልትሰማ እንደቻለች አልገባትም። ሉሲ የምትባለውንም ልጅ አላወቀቻትም። አብነት አልጋ አጠገብ ተቀምጣም እንደሚከተለው ልታስረዳት ሞከረች።

«አብነት» አለች ነርሷ፥ «ሕፃኑ ኢየሱስን በአካል ለማየት አትችይም። እርሱ የተወለደው ከብዙ ዓመታት በፊት ነበር። አሁን ወደ እግዚአብሔር

ሄዱል፥ ልጆቹ ግን የእርሱን ልደት መታሰቢያ እያከበሩ ነበር። የዘመሩትም እኛን ከኃጢአትና ከኀዘን ሊያድነን እንደመጣ አስታውሰው ነው። ስለ ኢየሱስ ዘርዝሬ እነግርሻለሁ። ያኔ በደምብ ይገባሻል እሺ?»

አብነት ጸጥ ብላ ተኝታ ታዳምጣለች፤ ዓይኖቿ ነርሷን ብቻ ይመለከታሉ። ስለ ሕፃኑ የበለጠ ለማወቅ ጓጓች፤ ስለ አንድ ጉዳይ ለማወቅ እንደዚህ ጓጉታ አታውቅም።

«ስሚ አብነት እግዚአብሔር ይወደናል» አለች ነርሷ «ስለዚህ ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚወስደውን መንገድ እንዲያሳየን ልጁን ኢየሱስን ወደ እኛ ላከው። እናቱ ቦታ ስላላገኘች በተወለደ ጊዜ በግርግም አስተኛችው። አሁን እርሱ ወደ እግዚአብሔር ሄዷል፤ ግን አልሞተም በሕይወት አለ። አሁንም ይወደናል። አናየውም እንጂ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር አለ። አሁንም ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚወስደውን መንገድ ሊያሳየን ይችላል።»

ነርሷ ይህንን ካብራራች በኋላ ሄደች። አብነት ግን ከተኛችበት አልተንቀሳቀሰችም፤ እንደተኛች በደብዛዛው መብራት ላይ ዓይኖቿን ተከለች። እዚያም ስለሰማችው ነገር ደጋግማ ታስብ ነበር።

አብነት መጀመሪያ ያሰበችው ወደ ፎቁ መውጣት፥ ሻማዎቹን ማየትና ለሕፃኑ ስጦታውን መስጠት፥ ከዚያም ሮጣ መመለስ ነበር። አሁን ግን ሁሉ ነገር ተለዋውጧል። ሕፃኑ እንደማይመጣ ተነግሯታል፤ ስለዚህ ልታየው አትችልም። ግን አብነት አላዘነችም፥

ምክንያቱም ነርሷ እንዲህ በማለት የተሻለውን ነገር ነግራታለች። «ይወድሻል! አይታይም እንጂ ሁልጊዜ ከአንቺ ጋር አለ። . . . ወደ መንግሥተ ሰማይ የሚወስደውን መንገድ ሊያሳይሽ ይችላል።»

ከዚያ በኋላ አብነት እንቅልፍ ወሰዳትና ሌላ ሕልም አየች። ሕልሙም እንደዚህ ነበር፤ በጨለማ መካከል ቀጭን ብርሃናማ መንገድ አየች። በመንገዱ መጀመሪያ ላይ የሚያምርና ብሩህ ዐይኖች ያሉት ሕፃን ቆሟል። በአንዱ እጁ የተለኮሰ ሻማ ይዞ ነበር። በሌላው እጁ ደግሞ አብነት እንድትከተለው ምልክት ሰጣት፤ ሕፃኑን በጣም ስለወደደችው ተከትላው ትሄዳለች። እጅ ለእጅ ተያይዘው ደረጃ ይወጣሉ። ለሕይወቷ የሚያስፈልጋትን ሁሉ እንዳገኘች ይሰማታል። ከዚህ በኋላ የሚያስፈራትና የሚጎዳት ነገር እንደሌለ ትረዳለች። በጣም ከመዋደዳቸው የተነሳም ማንም ሕፃኑን ከእርሷ ሊወስደው አይችልም፤ እርሷንም ከሕፃኑ የሚለያት የለም። ከእርሱ ጋር በመሆኗ ፍቅርና ደስታን አግኝታለች።

## ሁሉም ሻማዎች ሲለኮሱ

አብነት በመኪና ግጭቱ እግሯ ተሰብሮ ነበርና አንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን በሆስፒታል ቆየች። እዚያ የቆየችው ደስ እያላት ነበር። ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን እናቷ ሕፃኑን ወንድሟን አዝላ ልትጠይቃት ትመጣለች። ከምሽቱ አንድ ሰዓት ደግሞ በአካባቢው የሚኖር ወንጌላዊ ጊታር ይዞ ይመጣል። ኢየሱስ ሰው ሆኖ የሠራቸውን ታሪኮች ይነግራቸዋል። ከዚያ ሁሉም በአንድነት ይዘምራሉ።

አብነት ስለ ኢየሱስ መስማት ደስ ይላታል፤ በተለይም ለበሽተኞች መድኃኒት ሳይሰጥ እጁን ጭኖ በመጸለይ ብቻ እንዲድኑ ማድረጉ ይገርማታል። ሕፃናትንም ተቀብሎ፤ ባርኮና ደስ እንዲላቸው አድርጎ ልኳቸዋል።

አንድ ቀን ግን ወንጌላዊው እንዲህ በማለት አሳዛኝ ታሪክ ነገራቸው፤ «ኢየሱስ የሞት ፍርድ ተፈረደበት፤ እነዚያ በሽተኞችን ያዳኑ፥ ሕፃናትን የዳበሱ ርኅሩኅ እጆቹ በመስቀል ላይ በምስማር ተቸነከሩ። የሞተው ግን በፈቃደኝነትና በታዛዥነት እንጂ በግዴታ አልነበረም። ይህንንም ያደረገው የሰው ልጆች ሁሉ ለሠሩት ጥፋት ሲል ነው።»

አብነት ይህን ስትሰማ በጣም አዘነች፥ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ውሸት እንደምትናገር ታውቃለች፥ አንዳንዴም ትቆጣለች፥ ሕፃናቱን ትመታለች፥ እናቷንም አታከብርም።

በዚያ ሌሊት ደግሞ ሌላ ሕልም አየች፤ ኢየሱስ ወደ እርሷ እየመጣ ነበር። እጆቹ ቆስለዋል፤ ከዚህ የተነሳ የበፊት ጥፋቶቿ ሁሉ ይቅርታ ሊያገኙ እንደሚችሉ አመነች። ከዚህ በኋላ ሁሉን እንደ አዲስ መጀመር ትችላለች።

«ከዛሬ ጀምሮ ኢየሱስን እከተለዋለሁ» ስትል አብነት አንሾካሾከች፥ ሁለቱን ትናንሽ እጆቿን አጋጠማ።

ኢየሱስን ከልቧ ትወደዋለች፤ ስጦታም አዘጋጅታለት ነበር። ሉሲ ሻማዎቿን ስትለኩስና ስጦታዎቹን ስትጠቀልል ትዝ አለቻት። አብነትም

እንደ ሉሲ ሻማ ለመለኮስ ፈለገች፥ ግን አልቻለችም። የምትሰጠው ነገር የሌላት ተራና ድሃ ልጅ ናት።

አብነት ከጥቂት ጊዜያት በኋላ በምርኩዝ ድጋፍ መራመድ ቻለች። በአትክልት ስፍራው አካባቢ እግሯን ታፍታታ ነበር። አንድ ቀን ዋናው ሐኪም መጡና «ስለተሻለሽ ከሰዓት በኋላ በመኪናዬ ወደ ቤትሽ እወስድሻለሁ» አሏት።

ሐኪሙ ከሄዱ በኋላ አብነት ጋደም እንዳለች ስለመጪው ጊዜ ማሰብ ጀመረች። ወደ ቤቷ ለመሄድ በመቻሏ ብዙም ደስ አላላትም። በእርግጥ ሆስፒታሉና አካባቢውን ብዙ አትርቀውም፥ ምክንያቱም እህቷን እየያዘች እሁድ እሁድ እንድትመጣና የሰንበት ትምህርት እንድትማር ተፈቅዶላታል።

ሆኖም ለአንዲት ትንሽ ልጅ አንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን አጭር ጊዜ አይደለም። የሆስፒታሉን ንጽሕናና የአኗኗሩንም ሥርዓት በጣም ወዳዋለች። በእነርሱ መንደርና በእናቷ ቤት ይህ ሁሉ የለም። ፍየሎቹ፥ ሕፃናቱ፥ ድመቶቹ፥ ባልዲዎቹ፥ የከሰሉ ጢስ፥ የሚያፈሰው ጣራና ሌሎቹም ትዝ አሏትና በረዥሙ ተነፈሰች። በመሃሉ ነርሷ መጥታ «ወደ ቤትሽ ስለምትሄጂ ደስ ብሎሻል አይደል?» ብላ ስትጠይቃት አብነት መልስ አልሰጠቻትም።

ሐኪሙ ከምሳ በኋላ መጡ። እርሳቸውና አብነት ተያይዘው ሲወጡ ብዙ በሽተኞች ይሰናበቷት ነበር። አንዳንዶቹ «ብቅ እያልሽ ጠይቂን» ሲሏት፥ ሌሎች

ደግሞ «በሰላም ሂጂ አብነት፥ እግዚአብሔር ደስታን ይሙላብሽ» እያሉ መልካም ምኞታቸውን ገለጹላት።

አብነት የምትይዘው ሻንጣ አልነበራትም። ስለዚህ ሁለቱንም እጆቿን እያውለበለበች ተሰናበተቻቸው። ከዚያ በሐኪሙ መኪና ዳገቱን ወጥተው ወደ አብነት መንደር ተጓዙ።

ሐኪሙ ሰዎችን ለመጠየቅ ከነአብነት መንደር አልፈው መሄድ ነበረባቸው። ስለዚህ ቤቷ አጠገብ ስትደርስ አብነትን አወረዱትና ተሰናብተዋት ጉዟቸውን ቀጠሉ። አብነት ለጥቂት ጊዜ ቆም ብላ ዙሪያዋን ተመለከተች። አዳዲስ አበቦች በወንዙ ዳርቻ ፈክተዋል። ትናንሽ የበግ ግልገሎች በአካባቢው ይታያሉ። ልጆቹ ስላዩአት እየሮጡ ወደ እርሷ መጡ።

ከዚያ በኋላ የሆነው ሁሉ ደስ የሚል ነበር። ሁሉም ይንጫጩ፥ ያቅፋዋትና ይስሟት ነበር። እቤት ገብታ ቁጭ እንዳለች ትንሽ ወንድሟን ታቀፈችው። ሌላው ወንድሟ ከኋላ አንገቷ ላይ ተጠመጠመ። ግራና ቀኝ እህቷና ሌላ ወንድሟ ተቀመጡ። ትልቋ እህቷ ደስታዋን ለመግለጽ ትጨፍር ነበር። እናቷ ባለ ቅመም ሻይ አፈሉላት።


አብነት በጣም በጣም ደስ አላት፤ ከዚያም ጸጥታና ንጽሕና ያለበትን ሆስፒታልና አልጋዋን አስታውሳ ሳቀች። ከዚህ ፍቅር ከሞላበት ቤት ርቃ ስድስት ሳምንታትን ማሳለፍዋ ደንቃት፤ የእህቶቿና የወንድሞቿ ልፊያ እንደቀረባት አሁን ታወቃት።

የታቀፈችውን ሕፃን ቀስ ብላ ተመለከተችው፤ እንዲህ ዓይነት የሚወደድና ቆንጆ ሕፃን እንደሌለ አሰበች፤ ቤተሰቧንም በጣም እንደምትወድ ገባት። ለእነርሱ በፊት ከነበራት ፍቅር የአሁኑ በለጠ፤ ምክንያቱም ወዲያው ገባት።

ሌላውን ሕፃን ኢየሱስን አውቃዋለች፤ አሁን እርሱ በልቧ ውስጥ እየኖረ ነው። ዛሬ በዙሪያዋ ያሉትን ሁሉ የምታያቸው በግልጽነትና ጥልቀት ባለው በእርሱ ብርሃን ነው። በሰላም ተሞላች፤ ቤቷ በመመለሷም ደስ ብሏታል።

ልክ ከአራቱ ሻማዎች ይወጣ እንደነበረው ብርሃን ፍቅር፥ መልካምነት፥ ሰላምና ደስታ ከኢየሱስ ይመነጫሉ። እነዚህ ሁሉ ደግሞ አብነትን ብቻ ሳይሆን ጎጆውን፥ እናቷን፥ ልጆቿንም ሁሉ ይነካሉ። ከኢየሱስ ፍቅር የተነሳ ሁሉም ይኖራሉ።

# ትንሹ እንግዳ



## ትንሹ እንግዳ

### ጉብኝት

እትዬ በለጡ ከእንቅልፍ ነቁ። የብርሃን ጨረሮች በግድግዳው ስንጥቆች ዘልቀው መግባት ጀምረዋል። ዶሮዎቹም በማስካካት አካባቢውን ይረብሻሉ። ገና ዱሮ ነግቶ ቀን ሆኗል። እርሳቸው ግን አልጋቸው ላይ አርፍደዋል።

የግዳቸውን ቀስ ብለው ተነሡ፤ በሚቀጥሉት ጥቂት ሰዓታት ሊጠናቀቁ የሚገባቸው ብዙ ሥራዎች አሏቸው። ነገር ግን ከዶሮዎቹ ረባሽ ድምፅ የተነሳ ተረጋግተው ማሰብ አልቻሉም። አንድ ችግር ሳይገጥማቸው አልቀረምና ተንደርድረው በሩን ከፈቱ፤ ቀዝቃዛው ነፋስ በቀጥታ ፊታቸው ላይ ሲያርፍ ዐይናቸውን መጨፈን ግድ ሆነባቸው። ዶሮዎቹ ግን እያስካኩና እየሮጡ ወደ እርሳቸው መጡ፤ ዐይናቸውን ሲገልጡ ደግሞ የበለጠ የረፈደ መሰላቸው። ከወደ ኮረብታው አቅጣጫ ሰው መጥቶ እንደሄደ የሚጠቁም በፈጣን እግሮች የተረገጠ ዱካ አዩ። ወደ ዶሮዎቹ ቤት ልብ ብለው ሲመለከቱ የእንቁላል መጣያው ካርቶን ባዶ ነው። ይህ ሲያጋጥማቸው ለሁለተኛ ጊዜ ነው። ዐይኖቻቸው እንባ አቀረሩ፤ ትንሹ ሌባ ማን እንደሆነ አላወቁም፤ ቢሆንም ፈጥነው አንድ እርምጃ መውሰድ አለባቸው። ምክንያቱም የሚተዳደሩት ከእንቁላል ሽያጭ በሚያገኙት ገቢ ነው። በተለይ ሲመለሱ ኮረብታው የሚያደክማቸው ቢሆንም ለገበያው ቁልቁል መውረድ አልተሳናቸውም። ከዚህ በኋላ

ለምን ያህል ጊዜ ብቻቸውን መሄድና መመለስ እንደሚችሉ አያውቁምና የሚረዳቸው ሰው ያስፈልጋቸዋል፤ ግን ማንም ስለ እርሳቸው ግድ አልነበረውም። አንዲት ሴት ልጅ ብቻ ነበረቻቸው። እርሷም አድጋ ሀብታም ባለ ሱቅ አገባች፤ ሰውየው ደግሞ እትዬ በለጡ አብረዋቸው እንዲኖሩ አልፈለገም፤ አልፎ አልፎ ብቻ ጥቂት ገንዘብ ይሰጣቸዋል።

እትዬ በለጡ እንስራቸውን አዘሉና እያጉረመረሙ ወደ ውኃው ጉድጓድ ወረዱ። አሁን መሞቅ ጀምሯል፤ የፀሐይ ብርሃን በተሸበሸበው ፊታቸው ላይ ሲያርፍ ብርታትን ሰጣቸው። ወቅቱ ፀደይ ስለሆነ ሐምራዊ አበቦች በየስፍራው ይታያሉ።

ምንም እንኳ የእትዬ በለጡ ዐይኖች የፈዘዙ ቢሆንም፥ በዙሪያቸው የሚያዩት የተፈጥሮ ውበት ደስ አሰኛቸው። ትንሹን ሌባ ረሱት፤ ይልቁኑ የሚያስቡት ከሁለት ሰዓት በኋላ የምትመጣውን ናርዶስን ነበር። ያኔ የመጽሐፉን ቃል ታነብላቸዋለች፥ መጽሐፉም የእግዚአብሔር ቃል ነበር።

እንስራው ስለ ከበዳቸው ከጎጇቸው በር ሲደርሱ በጣም ደክሟቸው ነበር፥ ሆኖም ለማረፍ ጊዜ አልነበራቸውም፤ ሁሉ ነገር መዘጋጀት አለበት። ጀበናውን በከሰሉ ፍም ላይ ጣዱ። ለዳቦ የሚሆነውን ሊጥ ካቦኩ በኋላ ወለሉን መወልወል ጀመሩ። ምንጣፉን አጸዱ፥ ለዶሮዎቹ ጥሬ ሰጡ፥ ከዚያም የሚወዱትን የነሐስ ትሪ አጠቡ። ናርዶስ እስክትመጣ ድረስ መብላትም ሆነ መጠጣት አይችሉም፤ ለምን

ቢባል ሁለት ጊዜ ያን ለማድረግ የሚበቃ ገንዘብ የላቸውም። ግን ደስታቸው ብርቱ አድርጓቸዋል፤ ቅልል ብሏቸውና ጠንክረው ሥራቸውን ያከናውናሉ። በተለይ የዓርብ ቀን ሥራ የተለየ ነው፤ ድግስ የሚያዘጋጁ ይመስላሉ።

ሁሉ ነገር ከተዘጋጀ በኋላ ትንሿን ክብ ጠረጴዛ ወደ በሩ አስጠግተው አኖሩት፤ በላይዋ ላይ የቡናውን ጀበናና ብርጭቆዎች አስቀመጡ። ከዚያም ከአልጋዋ ሥር ያለውን ሳጥን ጎትተው ከውስጡ መጽሐፉን በአክብሮትና በሚንቀጠቀጡ እጆቻቸው አወጡ። ያረጀና ቀለሙ የለቀቀ ትንሽ መጽሐፍ ነበር። እናም ለአስራ አምስት ዓመታት ከእርሳቸው ጋር ኖሯል።

እትዬ በለጡ የኮረብታማው አካባቢ ነዋሪ አይደሉም። ያደጉትም ሆነ የተዳሩት በትልቅ ባሕር አጠገብ ባለች አነስተኛ ከተማ ውስጥ ነበር። በዚያም ብቸኛ ሴት ልጃቸውን ወለዱ። ልጃቸውም ገና ድክ ድክ ማለት ሳትጀምር በፊት ባላቸው ጥሏቸው ሄደ። ያላቸው አማራጭ ለአንዲት የውጭ አገር ሴት ተቀጥሮ መሥራት ነበር፤ ሴትየዋ ደግሞ በጣም ደግ ነበሩ። አንዳቸው የሌላውን ቋንቋ ስለማይችሉ በንግግር አሳባቸውን አልተለዋወጡም፥ ግን ሴትየዋ ርኅሩኅና ጨዋ እንደነበሩ እትዬ በለጡ ያስታውሳሉ። ሴትየዋ በመኝታ ጊዜ ከልጆቻቸው ጋር የሚያነቡት መጽሐፍ ነበራቸው። ለሰው ያላቸው ፍቅር ከዚህ መጽሐፍና ከእግዚአብሔር የተገኘ ይመስላል። አንዳንዴ ስለዚሁ ጉዳይ ሊያብራሩላቸው ቢሞክሩም እትዬ በለጡ ግን ለመረዳት አልቻሉም።

የሴትየዋ ባል ለአትዬ በለጡ ልጅ የትምህርት ቤቷን ክፍያ ይሸፍኑላቸው ነበር። ግን አስራ አምስት ዓመት ሲሆናት ሀብታሙን ነጋዴ አግብታ ሄደች። ከብዙ ጊዜያት በኋላ አንድ ቀን አሠሪዋ ሴትዮ ወደ አገራቸው ለመመለስ ማሰባቸውን በመግለጽ ሌላ ሥራ እንዲፈልጉ ለአትዬ በለጡ ነገሯቸው፤ ይህም አትዬ በለጡን በችግር ላይ ሃዘን ጨመረባቸው፤ የሴትየዋን ልጆች እንደ ራሳቸው ልጆች ያዩዋቸው ነበር። አሁን ግን የመለያየት ጊዜ ደረሰ፤ በዚህም ሃዘናቸው በረታ። ያጽናናቸው ነገር ቢኖር አንድ ብቻ ነበር። ከመለያየታቸው በፊት ሴትየዋ ለአትዬ በለጡ አንድ መጽሐፍ ሰጧቸው። መጽሐፉ በአትዬ በለጡ የመጀመሪያ ቋንቋ የተጻፈ ነበር።

«ይህ እኛ በየዕለቱ የምናነበው መጽሐፍ ነው። ስለ ኢየሱስና ወደ እግዚአብሔር ስለ መቅረብ ይናገራል። በጥንቃቄ ያዥው፤ የልጅ ልጆችሽ ሲያድጉ ደግሞ እንዲያነቡልሽ አድርጊ። ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው» ብለዋቸው ነበር።

በዚያኑ ቀን ከሰዓት በኋላ ሰዎቹ ወደ አገራቸው ሄዱ፥ አትዬ በለጡ በአውሮፕላን ወደሚሳፈሩበት ቦታ ሄደው እያለቀሱና እጃቸውን እያውለበለቡ ሸኟቸው። መጽሐፉን በመሐረባቸው ጠቅልለውና በሳጥናቸው ውስጥ ቆልፈው ወደ ቀድሞ ቤታቸው ተመለሱ። ከዚያም በኮረብታው አካባቢ ወደምትኖረው ሴት ልጃቸው ቤት ሄዱ።

ቤቷ ጠባብ ነበረች፤ ልጆቹ ደግሞ ዓመለኞችና መጮህ የሚወዱ ነበሩ። የልጃቸው ባልም አትዬ በለጡ አብረዋቸው እንዲኖሩ አልፈለገም። በዚያ ቦታ

እንደማያኖራቸው አቶ በለጡ ወዲያው ገባቸው። ስለዚህ ራቅ ብለው አሠሪያቸው በሰጧቸው ትንሽ ገንዘብ ጎጆ ቤትና ትንሽ መሬት ገዙ። ባለፉት አስራ አምስት ዓመታት የኖሩትም እዚህ ነው። ትንሽ የአትክልት ስፍራ አላቸው። ዶሮዎችንም ያረባሉ። ናርዶስ የእርሳቸው የልጅ ልጅ ስትሆን፥ ዕድሜዋ አስራ ሁለት ዓመት ሆኗል።

አቶ በለጡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ መጽሐፉን ለማንም አላሳዩም። በእርግጥ ሊያነቡትም አይችሉም። ልጃቸውን ወይም ሌሎቹን ልጆች እንዲያነቡላቸው ቢጠይቁ እንደሚስቁባቸው አይጠረጠርም።

አንድ ቀን ከልጅ ልጆቻቸው አንዱ እየሮጠ መጥቶ «እማማ በፍጥነት ነይ! እናታችን ሴት ልጅ ወልዳለች» አላቸው። ይህ በእርሳቸው ሕይወት ታላቅ ቀን ነበር፤ በመጪው ጊዜ ነገሮች እንደሚለወጡም አወቁ። በትንሿ ባለአጥር የሕፃናት አልጋ አጠገብ ጎንበስ ብለው የናርዶስን ብልህ ዐይኖች ተመለከቱ። አንድ ቀን እርሳቸውና ይህች ሕፃን አብረው ያንን መጽሐፍ እንደሚያነቡ በዚህም የእግዚአብሔርን ድምፅ እንደሚሰሙ በልባቸው አወቁ። ለዚህ አልቸኮሉም፤ ይልቁኑ በትዕግስት ጠበቁ። ልጅቱም ከመጀመሪያው አንስቶ አቶ በለጡን ትወዳቸው ነበር። ናርዶስ ባዘነች ወይም በታመመች ጊዜ እርሳቸው እንዲጠሩ ትጠይቃለች። በቤቷ ውስጥና ሌሎቹን ልጆች በመጠበቅ ሥራ የሚበዛባት እናቷም ቢያንስ ሴቷን ልጅ በማጽናናትና በማስታመም የሚረዳት በማግኘቷ ደስተኛ ነበረች። በተለይ በመጀመሪያዎቹ ስድስት ዓመታት ሕፃኗን

ለመንከባከብ ሲሉ እትዬ በለጡ ዶሮ ማርባታቸውን እንኳ ትተው ነበር። ናርዶስ አድጋ ትምህርት ቤት ከገባች በኋላ ነገሮች የዱሮ መልካቸውን መያዝ ጀመሩ፤ አንድ የተረፈ ነገር ቢኖር መጠያየቃቸው ነው። ሁልጊዜ እሁድ እትዬ በለጡ ወደ ልጃቸው ቤት ሲሄዱ ዓርብ ዓርብ ደግሞ ናርዶስ እትዬ በለጡን ልታይ ትመጣለች።

ናርዶስ አደገች፤ ቆንጆና ለግላጋም ነበረች። በትምህርቷ ያገኘችውን እድገት ለማሳየት በየሳምንቱ ደብተሮቿን ታመጣ ነበር። ዕድሜዋ 12 ዓመት ሲሞላ በሁለት ቋንቋዎች አቀላጥፋ ታነብ ነበር፤ ከአራት ወራት በፊት አንድ ቀን እትዬ በለጡ እየፈሩና እጆቻቸውም እየተንቀጠቀጡ መጽሐፉን አውጥተው ታሪኩን ለናርዶስ ተረኩላት። «ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፍቅር ይናገራል፤ ለ15 ዓመታት ሳጥኔ ውስጥ ደብቄው ነበር፥ ግን ፈጽሞ ላነበው አልቻልኩም» አሏት።

ከትምህርት ቤት መጽሐፎቿ ሌላ ምንም የሌላትና ማንበብ የምትወደው ናርዶስ በዚህ ተደሰተች፥ ወዲያውኑ ትመረምረው ጀመር። በታሪኮቹም በጣም ስለ ተሳበች አሮጊቷ በዝምታ ያስተውሏት ነበር። ያን ሥዕል እስከ መቼውም አትረሳውም። ናርዶስ በደብዛዛው የክረምት ፀሐይ ብርሃን እየታገዘች ከበሩ አጠገብ ተቀምጣ ጮክ ብላ ማንበብ ጀመረች፤ በመጨረሻ ቀና ስትል ዐይኖቿ ያበሩ ነበር።

«ጥሩ መጽሐፍ ነው፥ አያቴ! አብረን እናነበዋለን፤ በየሳምንቱ አንድ ምዕራፍ አነብልሻለሁ» አለች ናርዶስ። ከዚያም ስማቸውና ተሰናብታቸው ሄደች።

እትዬ በለጡ ግን የፀሐይን መጥለቅ እየተመለከቱና ከመጽሐፉ የሰሙትን እያሰላሰሉ ለረዥም ጊዜ ተቀመጡ፤ በተለይም «እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ» የሚለው ዐረፍተ ነገር በአእምሮአቸው ተቀርፆ ቀርቷል። ከዚያ ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ትንሿን ጎጆ የሚያደምቅ ወዳጃቸው ሆነ፤ እርሱ ማን እንደነበረም ይሁን ስለ ሞቱና ትንሳኤው አያውቁም ነበር። ነገር ግን አሁን አስፈላጊና ሕያው አካል መሆኑን በልባቸው ማመን ቻሉ። ዘወትር ዓርብ በመጽሐፉ በኩል ደግሞ ይናገራቸው ጀመር።

«እንደምን ዋልሽ አያቴ? ገና ምሳ ሰዓት ሳይደርስ ተኝተሻል እንዴ?» አለች ናርዶስ።

እትዬ በለጡ ቶሎ ብለው ተንቀሳቀሱ። ከዚያም ከበሩ ላይ የቆመችውን ናርዶስን ተመለከቷት። በእርግጥ አልተኛችም፤ ግን ስላለፉት ዘመናት እያሰበችና እያሰላሰለች ነበር። ናርዶስ በሩጫ የመጣችው እየሳቀች ነበር። የሞቀ ሰላምታ ተለዋወጡ፤ ዳግመኛ አብረው መሆን ስለቻሉም ደስ አላቸው።

ዓርብ ሲገናኙ መጀመሪያ ቁርሳቸውን ይበላሉ። ብዙ ጊዜ ከዳቦ ጋር የሚቀርብ ቡና አይኖርም፤ እትዬ በለጡ ያንን ለመግዛት አቅም የላቸውም። በሚኖር ቀን ደግሞ የሚያፈሉትም ሆነ የሚቀዱት በጥንቃቄ ነው። በዚህ ጊዜ ናርዶስ እግሮቿን አጠላልፋ በመቀመጥ በሳምንቱ ውስጥ ያጋጠማትን ታወራላቸዋለች። ናርዶስ ደስ የምትልና ነገሮችን ለሰዎች በሚገባ መንገድ መግለጽ የምትችል ወጣት ናት።

ዛሬም እንዲህ ትላቸው ጀመረ «ባለፈው ሰሞን በጎረቤታችን የምትኖር ሴት ወልዳ ነበር። ሄጄ እንዳያት ተፈቀደልኝ፤ አባቴም ረዥም ባለጥልፍ ቀሚስ ገዛልኝ፤ ይህም እሁድ አንቺ ልታይኝ ስትመጪ እንድለብሰው ተብሎ ነው። ወንድሞቼ አዲስ ልብስ ያስፈልገናል በማለት ተከራክረው ነበር፤ አባዬ ግን እንዲቆዩ ነገራቸው። ወንዙ ሞልቶ አካባቢውን ከማጥለቅለቁም በላይ ሁለት ፍየሎችን ወሰደ፤ ባለቤቶቻቸውም ጉዳዩን ለከተማዋ አስተዳደር እናመለክታለን ብለዋል። የአክስቴን ልጅ ቤት ጣሪያ ነቅሎ የገባው ሌባም የወርቅ ጌጣጌጦችን ሰርቆ አምልጧል።»

ልክ እዚህ ላይ ስትደርስ አሮጊቷ የእርሳቸውን ቤት የሚዘርፈውን ሌባ አስታወሱ። ለናርዶስም እንዲህ አሏት «ለቁርስ እንቁላል ልጠብስልሽ ፈልጌ ነበር፤ ግን ያ ትንሽ ልጅ ለቃቅሞ ወሰደብኝ። ልብሱ የቆሸሸና በባዶ እግሩ የሚሄድ ነው፤ ግን በኃይል ይሮጣል።»

ናርዶስ አሳቢነቷን በሚያመለክት ሁኔታ አንገቷን ነቀነቀች፤ ከዚያም «ምናልባት ረዘነ ሳይሆን አይቀርም» አለች። በመቀጠልም «አባቱ ሞቷል፤ እናቱም ሌላ ባል አግብታ ትታው ሄዳለች። እንጀራ አባቱም አብሯቸው እንዲኖር አልፈለገም። ስለዚህም በኮረብቶቹ ላይ እየተንከራተተ የሚኖር ሲሆን በእርሻ ውስጥ ይሠራል፥ ግን ብዙ ጊዜ ወደ ከተማ አይመጣም። ምናልባትም ተይዞ ወደ መጠለያ እንዳይላክ ይፈራ ይሆናል። ግን እኮ ማንም ሰው የአንቺን እንቁላል ሊሰርቅ ይችላል አያቴ፤ ስለዚህ

ኃይለኛ ውሻ ያስፈልግሻል» በማለት ተናገረች ናርዶስ።

«ግን ምን አበላዋለሁ? ለራሴም የምበላው አላገኘሁ።»

«አባባን እጠይቀዋለሁ» አለች ናርዶስ። ከዚህ የበለጠና ይህን ችግር ማለፍ የሚቻልበት መንገድ አልታያትም። ይህን ያለችው በሹክሹክታ ነበር። ከዚያም በረዥሙ ተነፈሰች። ትንትናዋን ለመግለጽ እንጂ ጥያቄዋ ምንም ለውጥ እንደማያመጣ ታውቃለች። ሀብታሙ አባቷ ለአሮጊት አያቷ ግድ የሌለው መሆኑ ሁልጊዜም ያስገርማታል።

አትዬ በለጡ ግን አንድ ነገር አስታወሱ፤ የዕለቱ ዋነኛ አጋጣሚ እየቀረበ ነው። ናርዶስ የቁርስ ዕቃዎቹን ሁሉ አነሳች፥ አትዬ በለጡ ፍርፋሪዎቹን ጠረጉ፤ እናም ተዘጋጁ። የበሩን መጋረጃ ከጋረዱ በኋላ በቤቱ ጥግ ተደላድለው ተቀመጡ። ከዚያ ናርዶስ መጽሐፉን ከፈተች።

«ዛሬ የማነበው ምዕራፍ አስራ ስምንትን ነው አያቴ» አለች ናርዶስ፥ «ምዕራፍ አስራ ሰባት ስለ ምን እንደሚናገር ትዝ ይልሻል?»

አትዬ በለጡ መጽሐፉን በጣም ይወዱታል፥ ግን ማስታወስ የሚችሉት በጣም ጥቂቱን ነው። ይህ ናርዶስን በጣም ያስገርማታል፤ በእርግጥ አሮጊቷ ብዙም ለመያዝ አይሞክሩም።

ናርዶስ እንደ ዝማሬ በሚጣፍጥ ድምፅ ፈጠን ብላ ታነባለች፤ እናም አብዛኛው ወደ አሮጊቷ ጆሮ

ይደርሳል። ነገር ግን በየሳምንቱ ሊይዟቸው የሚችሉት እንደ ዕንቁ ያሉትንና ውድነቱን የሚያመለክቱት ቃላትን ብቻ ነው። ይህም ሳምንቱን ሙሉ ከአእምሯቸው አይጠፋም፤ ከዚህ ሌላ ግን ቃላቱ ይምታታባቸዋል። «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ» የሚሉት ዓይነት ዐረፍተ ነገሮችን ማለዳ ከእንቅልፋቸው ሲነቁ እንኳ ትዝ ይላቸዋል። በጎጇቸውም ውስጥ ሆነ በአትክልት ስፍራቸው ሲሠሩ ያበረታቷቸዋል፤ እነዚህ ቃላት ለእርሳቸው እንደ ውድ ዕንቁ ነበሩ። ውኃ ለመቅዳት ሲወርዱም እነኚህኑ ቃላት በቀስታ ይናገራሉ፤ ሸክሙም እንደ ዱሮው አይከብዳቸውም።

ዓርብ ዕለት ግን ያወቋቸውን በአእምሮአቸው ይይዙና አዲስ ለመስማት ይዘጋጃሉ፤ ደግሞም ያገኛሉ። መጽሐፉ ሁልጊዜም አዲስ ቃል አለው።

ንባቡ ከመጀመሩም በፊት የሚያስታውሱትን ለናርዶስ እንዲህ እያሉ ይናገራሉ፤ «ኢየሱስ ወደ ተራራ ወጣ፥ ፊቱና ልብሶቹም እንደ ፀሐይ አበሩ። እግዚአብሔር «ይህ ልጄ ነው» አለ። ደግሞ «በአፉ ገንዘብ የያዘ አንድ ዓሣ ነበር።»

«ሌላስ አያቴ?»

«ሌላ ትዝ አይለኝም። ይህም በቂ ነው። ቅድም ያልኩትን ብሩኅነት ግን ሳምንቱን ሙሉ ዐይቼዋለሁ። በልቤ እንደ ፍቅር ያበራ ነበር፤ ዛሬስ ምን ልስማ?» አሉ እትዬ በለጡ።

ናርዶስ በረዥሙ ተነፈሰች፤ የአያቷ የደከሙ ዓይኖች በጉጉት አተኩረው ያዩአታል። የሚቀጥለውን ምዕራፍ ፈልጋ ማንበብ ጀመረች። በልቧም «እንዴት ያለ እርስ በርሱ የሚቃረን መጽሐፍ ነው?» ስትል አሰበች። ያለፈው ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔር ክብር የሚናገር ነበር። በዚህ ሳምንት ደግሞ ስለ ትናንሽ ልጆች፥ ስለ ጠፉ በጎችና ስለሚጣሉ ሠራተኞች ይተርካል። አንድ ቅዱስ መጽሐፍ ለእነዚህ ተራ ነገሮች ቦታ መስጠቱ የሚደንቅ ነው።

እትዬ በለጡ ከንባቡ አንድ የሚያስደንቅ ቃል ካገኙ በኋላ መስማታቸውን ያቆማሉ፤ የምዕራፉን መጨረሻ አይጠባበቁም። ናርዶስ ይህንን አትረዳም ነበር፤ ዛሬ ግን ይህን የምታውቅበት አጋጣሚ ተፈጠረ። ናርዶስ በእግሯ ነካ አድርጋ እስክትጠራቸው ድረስ እትዬ በለጡ አንድ ዐረፍተ ነገር ይዘው እርሱን በማሰላሰል በአሳባቸው ርቀው ሄደው ነበር።

«አያቴ ሰማሽ? የዚህ አገልጋይ ታሪክ አስገራሚ አይደለም? ወደ እስር ቤት መግባቱ ትክክል ይመስለኛል።»

«እስር ቤት መግባት?» አለች አሮጊቷ «ማን ነው እስር ቤት የገባው ልጄ?»

«ለካስ አትሰሚም አያቴ? በዝግታ አሳምሬ አነበብኩልሽ፥ ግን ማዳመጥሽን እንጃ» አለች ናርዶስ ብስጭት ብላ።

«እያንዳንዱን ቃል ሰምቻለሁ፤» በማለት መለሱላት አሮጊቷ። «ስታነቢ የነበረው ስለ ትናንሽ

ልጆች ነበር --- ‹ሕፃኑን ብትቀበሉ እኔን እንደተቀበላችሁኝ ይቆጠራል› --- ግን ይህ ምን ማለት ነው የእኔ ልጅ?»

ናርዶስ ግን በታሪኮቹ ደስ ከመሰኘት በቀር ስለዚህ ጉዳይ የምታውቀው ነገር የላትም። ይሁንና ጓደኛውን ይቅር ማለት ያቃተው አገልጋይ ታሪክ ደስ ብሏታል፤ ለአያቷ ደግማ ነገረቻቸው። ታሪኩንም ግልጽ አድርጋ በእንቅስቃሴም አጅባው ነበር። ከዚያም በታሪኩ ውስጥ ያዩትን ክፉና መልካም ድርጊቶች አስታውሰው በመነጋገር ብዙ ተጫዋወቱ። በመጨረሻም ናርዶስ የዛፎቹ ጥላ እግሯ አጠገብ መድረሱን ተመለከተች፤ ይህ ደግሞ ፀሐይ ልትጠልቅ መሆኑን ያሳያል።

«መሄዴ ነው አያቴ» አለችና ወደ ጉድጓድ በማምራት ውኃ ቀዳች፤ ተመልሳም የአያቷን ሁለት ጉንጮች በየተራ ስማ እሁድ እንደምትመጣም አረጋግጣ ወደ ቤቷ ተጓዘች። እትዬ በለጡም ናርዶስ ከዐይንዋ እስክትሰወር ድረስ ይመለከቷት ነበር።

አሁን እትዬ በለጡ ብቻቸውን ናቸው፤ በሳምንቱ ውስጥ ከሚወዷቸው ጊዜያት አንዱ ይሄ ነው። ልክ ናርዶስን እንደሚወዷት ሁሉ ለብቻቸው ሆነው ሰማዩ ሲጨልም ማየትን ይወዳሉ፤ እጆቻቸውን በጭናቸው ላይ አስደግፈውና በሩ ላይ ተቀምጠው የሰሟቸውን ያሰላስላሉ። ለሕይወታቸው አዲስ እውቀትን የሚሰጥ አስደናቂና አዲስ ነገር እንደተማሩ ተሰምቷቸዋል፥ ግን ያንን ታሪክ እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉት አልገባቸውም።

«ትንሽን ልጅ የሚቀበል እኔንም ይቀበላል» በማለት ኢየሱስ ተናግሯል። የእርሱ ስም ትርጉም ደግሞ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው። እትዬ በለጡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ አልገባቸውም፤ ኢየሱስ ወደ እርሳቸው እንደመጣ ግን ገብቷቸዋል። ምክንያቱም ሰላም አግኝተዋል፤ መጽናናትና ጥበቃ እንደ ተደረገላቸው ይሰማቸዋል። በዚህ የክረምት ምሽት ኃይለኛ ነፋስ ጎጇቸውን ሲያንቃንቅ እንኳን አልፈሩም። ዛሬ የሰሟቸው አዲስ ቃላት ደግሞ ትንሽን ልጅ ቢቀበሉ ኢየሱስን እንደተቀበሉ እንደሚቆጠር ይናገራሉ።

«ግን የትኛውን ልጅ? እርሱስ የት ነው ያለው?» ብለው አሰቡ እትዬ በለጡ፤ በኮረብታማው አካባቢና በእርሻዎቹ ውስጥ ልጆች ሞልተዋል። ንፍጣቸውን አስሬ እየጠረጉ በዙሪያቸው ይንጫጫሉ፤ አንዳንዴም ዶሮዎቻቸውን እያባረሩ ወይም አትክልታቸውን እየረጋገጡ ያናድዱቸዋል። «መቼም ልጅ ሲባል ከእነዚህ አንዱ ሊሆን አይችልም?» አሉ እትዬ በለጡ በአሳባቸው።

ይህንኑ እያሰላሰሉ በመቆየታቸው ደከማቸው፤ አየሩ መቀዝቀዝ ጀምሯል። ሰማዩ በደመና እየተሸፈነ ነው፤ ምናልባትም ቆይቶ ሊዘንብ ይችላል።

እትዬ በለጡ ወደ መኝታቸው ሄደው ጋደም አሉ። ለጥያቄያቸው ምናልባት ነገ መልስ ማግኘት እንደሚችሉ አሰበዋል። መጸለይ አይችሉበትም፥ ግን በጣሪያው ቀዳዳ ኮከቦችን እያዩ ደህና ነገር ያስባሉ፤ ይመኛሉ።

በዚያ ምሽት ግን ከዋክብት አልነበሩም፤ ኃይለኛ ዝናብ ዘነበ። የአሮጊቷ ብርድ ልብስ ያረጀ ስለሆነ ከምሽቱ ብርድ አላዳናቸውም። ስለዚህም ይንቀጠቀጡ ነበር። በዚህ ላይ ቁርጥማት ስለተነሳባቸው ያቃስታሉ። ጥቂት ይተኙና ወዲያው ይነቃሉ፥ ግን እንቅልፍ በወሰዳቸው ቁጥር አንድ ልጅ በሕልማቸው ያዩ ነበር። ልጁ እንደ ናርዶስ ብሩህ ዐይኖች ቢኖሩትም ከዝናቡ የሚጠለልበት ቤት ስለሌለው ለመፈለግ ይንከራተታል።

## ልጁ

ዶሮዎቹ በጣም ከመንጫጫታቸው የተነሳ አትዬ በለጡ ባይነቁ ኖሮ እስከሚረፍድ በተኙ ነበር። ምክንያቱም ሊነጋጋ ሲል ኃይለኛ እንቅልፍ ወስዷቸው ነበር። የሌሊቱ ብርድ ስለመታቸው ቶሎ መንቀሳቀስ አልቻሉም። ጣራው ዝናብ ያንጠባጥብ ስለ ነበር ቤቱ በጣም ቀዝቅዟል። ያ ደግሞ ያስላቸዋል። እንደ ምንም ብርድ ልብሳቸውን ተከናንበው በጭቃ ላይ እየተራመዱ ዶሮዎቹ ቤት ሲደርሱ መጮኻቸውን አቁመው ነበር፤ የእንቁላል መጣያው ካርቶን ግን ባዶ ነው።

እትዬ በለጡ ስላዘኑ ጥራጥሬ በተሞላ ጆንያ ላይ ተቀምጠው ማልቀስ ጀመሩ፤ ምን ማድረግ እንዳለባቸውም አያውቁም። ይህ ሌባ ነገም በጠዋት እንደሚመጣ ጥርጥር የለውም። ምን የሚከለክለው አለ? እርሳቸው ሌሊቱን ሙሉ እዚያ ተቀምጠው ሊጠብቁ አይችሉም። ፖሊሶችም ቢሆኑ ስለ አንዲት አሮጊትና በየቀኑ ስለሚሰረቁ አምስት እንቁላሎች

ግድ አይኖራቸውም። ትልቅ ውሻ ቢኖራቸው ጥሩ ነበር፤ ግን ምን ያበሉታል?

እንደዚህ ቀን ብቸኝነትና ረዳት የለሽነት ተሰምቷቸው አያውቅም። «በዚህ ዓይነት ልቀጥል አልችልም፤ የሚረዳኝ እፈልጋለሁ» አሉ እትዬ በለጡ ጮክ ብለው። የራሳቸው ድምፅ አስደነገጣቸው። ለማን ነው የተናገሩት? ለዶሮዎቹ ወይም ለራሳቸው አልነበረም፤ ነገር ግን በዶሮዎቹ ቤት ለነበረና ለሰዎች ለሚያዝን ሌላ ሰው እንደተናገሩ ተሰምቷቸዋል። ስለ ጸሎት ምንም የማያውቁ ቢሆንም ንግግራቸው ጸሎት ነበር። ነገሩ የገባቸውም ይሄኔ ነበር።

በመጽሐፉ በኩል ለሚናገራቸውና በብርዳማው ምሽት ለሚያጽናናቸው ለኢየሱስ ነው የተናገሩት፤ እርሱ ደግሞ መስማት ይችላል። ይህን መረዳታቸው ደስታን አስገኘላቸው፤ ከአሁን በኋላ ሁልጊዜም ፍርሃታቸውን፥ ብቸኝነታቸውንና ረዳት የለሽነታቸውን ሊነግሩት ይችላሉ። ከዚህ ብልጭ ካለላቸው እውቀት የተነሳም ልክ ሸክሙን እንዳወረደ ሰው ቀለላቸው።

ለረዥም ጊዜ እዚያው ተቀምጠው ቆዩ፤ ከዚያም አንድ ነገር አሰቡ። አሳቡ በጣም ጉልህ ሆኖ ከመታየቱ የተነሳ ‹ተነሺ፥ ሂጂና እንቁላል የሰረቀውን ልጅ ፈልጊው› ብሎ አንድ ሰው የተናገራቸው መሰላቸው።

ይህን ነገር በተደጋጋሚ አሰቡ፤ ደጋግመው ባሰቡ ቁጥርም ስለ ጉዳዩ አስፈላጊነት ተረዱ፤ እዚህ ቁጭ ብለው በየቀኑ ቢሰረቁ ምን ይጠቅማቸዋል? ናርዶስ

እንኳ ልጁን እንደምታውቀው ተናግራለች። ባለፉት ዓመታት አንድም ቀን ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄደው አያውቁም፤ አሁንም መሄድ አልፈለጉም። ግን የናርዶስ አባት ሄዶ ስለ ጉዳዩ ሊያመለክት ፈቃደኛ ከሆነ ልጁ ተይዞ ሊታሠር ይችላል።

ስለዚህ ሌባ ልጅ ባሰቡ ቁጥር በክስ ይጨብጣሉ፤ በእርግጥ ፊት ለፊት አይተውት አያውቁም። ግን ይህን ስርቆት ለማቆም የሚረዳቸው ሰው ያስፈልጋቸዋል።

ዶሮዎቹ ቶሎ ቶሎ እንዲበሉ አደረጉ፤ የቀረውን ሥራ ቀስ ብለው ሊሠሩት ይችላሉ። የረጠበውን የቤቱን ወለል ወልውለው ሲያበቁ ውኃ ሊቀዱ ይሄዳሉ፤ መጀመሪያ ግን ይሄ ልጅ በሌብነት መጠየቅ አለበት። ማታ የተነሳባቸው ቁርጥማት አልተዋቸውም። ወደ ዋናው መንገድ የሚያደርሳቸው አቧራማ መንገድ ጨቅይቷል። ዝናቡ አሁንም ያካፋል፤ እትዬ በለጡ ግን ስለ ተበሳጩ ለመሄድ ተነሡ።

መጀመሪያ ላይ አንድ እርምጃ ወደ ፊት ሁለት እርምጃ ወደ ኋላ የሚሄዱ ይመስል ነበር። በጭቃው ተለውሰው እንደ ምንም ለመራመድ ተጣጣሩ። አንዳንዴም የወይራ ዛፎችን ግንድና ቅርንጫፍ እየተደገፉ ወደፊት ሄዱ። ሜዳውን ጨርሰው ኮረብታውን መውጣት እንደ ጀመሩ አንድ የተተወ እርሻ አጠገብ ደረሱ። በዚያም ሰብሉን ከወፎችና ከሌሊት አራዊት የሚጠብቁ ሰዎች ያድሩበት የነበረ፥ ግድግዳው የፈረሰና ጣሪያው የወደቀ ጎጆ አገኙ።

ከዝናቡ ለመጠለል ወደዚያ ቢገቡም ውስጡ የጨቀየና ተጠግኖ የማያውቅ ነበር።

ጥቂት እንደ ቆዩ ከዚሁ እንደ ምንም /ተደጋግፎ/ ከቆመ ቤት ውስጥ የሳል ድምፅ ሰሙ። ይሄኔ ጸጥ ብለው አዳመጡ፤ የሚንሾካሾክና ሳል የያዘው ሰው ያለ ይመስላል። ምናልባት የታመመ ውሻ ወይም ቀበሮ ይሆናል። ምክንያቱም በዚህ ፍርስራሽ ውስጥ ሰው ሊኖር አይችልም። ይህ ድምፅ ስላስፈራቸው አትዬ በለጡ ተንቀጠቀጡ፤ ስለዚህም ወጥተው መሄድ ጀመሩ። ነገር ግን ገና ጭቃውን ከመርገጣቸው ድምፅ ሰምተው ቆም አሉ። የሰሙት ልቅሶ ኃይለኛ ቢሆንም የእንስሳ አይመስልም፤ የታመመ ወጣት ልጅ የሚያሰማው ድምፅ እንደሆነ አልተጠራጠሩም።

እየተጠነቀቁ፥ ፈራ ተባ እያሉና ለየት ያለ ነገር ካጋጠማቸውም ለመሮጥ እየተዘጋጁ ወደ በሩ ተመለሱ። በመጀመሪያ ከጨለማው የተነሳ ምንም አላዩም፤ ኋላ ዐይናቸው ሲላመድ ግን በተከመረ ገለባ ላይ የተኛ ነገር ተመለከቱ። ፊቱ በእጁ ተሸፍኗል፤ እንቅልፍ የወሰደው ቢመስልም አንዳንዴ ይስላል፤ ደግሞም ያለቅሳል። አትዬ በለጡ ቆመው ሲያዩት ከቆዩ በኋላ ምንም የሚያስፈራቸው ነገር እንደሌለ ተረዱ፤ ውሻ ወይም ቀበሮ ሳይሆን የታመመ ልጅ ነበር።

በመሬቱ ላይ እየተራመዱ ቀስ ብለው ወደ ገለባው ተጠጉ። ከዚያም እጃቸውን በልጁ የተበጫጨቀ ልብስ ላይ አሳረፉ፤ ልጁም የሆነ ነገር እንደነካው ሲረዳ ዘልሎ ተነሳ። አትዬ በለጡን ሲያይ ደግሞ ወደ ኋላው

አፈገፈገ። ገና ዘጠኝ ዓመቱ ነው። ከሲታና በጣም የቆሸሸ ሲሆን ፊቱም ከትኩሳቱ የተነሳ ቀልቷል።

«ምን ሆነሃል ልጄ? ለምን እዚህ ተኛህ? ቤትህስ የት ነው?» ብለው ጠየቁት እትዬ በለጡ።

«ቤት የለኝም» አለ ልጁ ፍርሃቱ ከለቀቀው በኋላ «በጎች እጠብቃለሁ፣ የምኖረውም እዚህ ነው።»

«ብቻህን?»

አዎን ለማለት ራሱን አወዛወዘ።

«ውኃ ስጡኝ» አለ ጥቂት ቆይቶ።

ወደ ውጭ ወጥተው ባገኙት ሰባራ ሸክላ የዝናቡን ውኃ፣ ልጁ ያመጡለትን ውኃ እየተስገበገበ ከጠጣ በኋላ አፍጥጦ እያያቸው እንደገና መሳልና መንቀጥቀጥ ጀመረ።

የለበሱትን ጋቢ አውልቀው ለእርሱ አለበሱት፣ ከዚያም ቁጭ ብለው ዐይን ዐይኑን ያዩት ጀመረ። እንዲረዳው የተላከ መልአክ ወይም ሴት አያቱን መሰሉት። አያቱ ከመሞታቸው በፊት በጣም ይወዱት ነበር።

«ከእኔ ጋር ሁኑ ጥለውኝ አይሂዱ» አለ ልጁ።

ያላቸውን እያሰቡ ይመለከቱት ጀመር። ንግግሩ አንድ ነገር አስታውሷቸዋል፥ ግን በተሟላ መልኩ አይደለም፣ ቀስ በቀስ ግን እነዚያ ቃላት መጡላቸው «ጥለውኝ አይሂዱ – – – ተቀበሉኝ፣ ልጅን የተቀበለ ኢየሱስን እንደተቀበለ ይቆጠራል።» ምናልባትም ያ ልጅ ይሄ ሊሆን ይችላል። ይህንን

ልጅ ለመቀበልና ለመውሰድ ምንም አስቸጋሪ ነገር አይኖርም፤ መጠለያ፥ ምግብና ውኃ ያስፈልገዋል። ሰውነቱና ልብሱም ቆሽሿል። ከመጽሐፉ የሰሙትን በሥራ ላይ ለማዋል ጊዜው አሁን እንደሆነ ተሰማቸው።

«ቤተሰብ የለህም?» ብለው ጠየቁት።

«አባቴ ሞቷል» አለ ልጁ። በመቀጠልም «እናቴም ሌላ ባል አገባች፤ እንጀራ አባቴ እርሷንና ልጆቻቸውን ይዞ ወደ ትውልድ መንደሩ ሄደ። እኔን ግን አንድ ሰው ጋ በአደራ ተዉኝ፤ ሰውዬው እየደበደበ ሲያበሳጨኝ ከቤቱ ወጣሁ።»

«አሁንስ» ሲሉ ጠየቁት እትዬ በለጡ።

«አንድ በጎችና ፍየሎችን የሚጠብቅ ሰው አለ። እርሱን እረዳዋለሁ፤ ምግብና ትንሽ ገንዘብ ይሰጠኛል። እዚህ እተኛለሁ። ዛሬ ግን ተነስቼ ወደዚያ ልሄድ ስል ራሴን አዞረኝ፤ ስለዚህ ተመልሼ ተኛሁ።»

«ይሄ ቤት በጣም ይበርዳል» አሉ አሮጊቷ በጣም እያሰቡ። «ከእኔ ጋር ወደ ቤቴ ብንሄድ ይሻላል። ምግብ ትበላለህ፥ ብርድ ልብስ ለብሰህም እሳት ትሞቃለህ።»

ልጁ ፈጥኖ ወደ እትዬ በለጡ ተጠጋ፤ በዚህ ጊዜ ግን ሦስት እንቁላሎች ከልብሱ ሥር ተንከባለሉ። እርሳቸውም ወዲያውኑ እንቁላል የሚሰርቃቸው ልጅ ይሄ እንደሆነ አወቁ፥ ግን አልተናደዱም፤ እንቁላሎቹን ቀስ ብለው ከመሬት አነሱ። ሌሎች ሦስት እንቁላሎችን ደግሞ ከገለባው ሥር አገኙ።

ሁሉንም በመቀነታቸው ቋጠሩ። ይህን ጊዜ ልጁ ማልቀስ ጀመረ። ምናልባትም ያገኘውን ጥሩ ዕድል በዚህ ምክንያት የሚያጣ መስሎት ይሆናል።

እትዬ በለጡ ግራ ገባቸው፣ ልጅን መቀበል ጌታ ኢየሱስን እንደ መቀበል እንደሆነ አምነዋል፣ ግን ይሄ ልጅ ደግሞ ሌባ ነው። ያም ሆነ ይህ ልጁ ይሄ ስለሆነ በአስቸኳይ መኖሪያ ማግኘት አለበት።

በመቀጠልም «ና እንሂድ፣ እየደገፍኩ እወስድሃለሁ። የእኔ ጎጆ የት ጋ እንደሆነ ታውቀዋለህ አይደል?»

አፍጥጦ አያቸው። አላመናቸውም፣ ማንንም አያምንም። ምናልባት አባብለው ወስደው ለፖሊስ ቢሰጡትስ? ግን እንዲህ የሚያደርጉ አይመስልም። በፊታቸው ላይ ንዴት አይታይም። በዚህ ላይ በዕድሜ የገፉ ርኅሩኅና ግልጽ ናቸው። በዓለም ካሉት ከምንም ነገሮች ይልቅ ከእርሳቸው ጋር መኖርን ፈለገ።

«በል እንሂድ፣ ዝናቡ ከባድ አይደለምና ፈጠን ብለን እንራመድ» አሉ እትዬ በለጡ።

ልጁ የአሮጊቷን ጋቢ እንደለበሰ ለመሄድ ጥረቱን ቀጠለ፣ ተያይዘው ወደ ጭቃው መንገድ ገቡ። እርሳቸው እንቁላሎቹን አጥብቀው ሲይዙ እርሱ ደግሞ እርሳቸውን ያዘ። ቶሎ ቶሎ ያስለው ነበር። እትዬ በለጡ ቤት ሲደርሱም መንቀጥቀጡ ጨመረ። ቶሎ ብሎ በምንጣፉ ላይ ተኛና አሮጌውን ብርድ ልብስ ለበሰ፣ ወደ ቤተሰቦቹ ቤት የተመለሰ ነው የመሰለው።

እትዬ በለጡ አሁን ኢየሱስ የላከውን ልጅ ለመቀበል ዝግጁ ነበሩ። ውኃ ቀዱ። ከዚያም የተረፋቸውን ከሰል በሙሉ አቀጣጥለው በጨለማው ክፍል ላይ ሙቀትን ፈጠሩበት። ዳቦ ጋገሩ፤ ማስቀመጫውን አራግፈው ቡና ካፈሉ በኋላ ሁለት እንቁላሎችን ጠበሱ፤ ስለ ነገ አልተጨነቁም። ዛሬ እዚህ ቤት ታላቅ እንግዳ ስለመጣ የተገኘው ሁሉ ለእርሱ መቅረብ አለበት። እጆቹንና ፊቱን ካጠቡት በኋላ አበሉት፤ አጠጡት። ከዚያም አንድ ጊዜ ሳል ይዟቸው ሐኪም ያዘዘላቸውን መድኃኒት ሞቅ አድርገው ሰጡት። ልጁ ተደሰተ፥ ተደነቀ፥ ሞቀው። በመጨረሻም እንቅልፍ ወሰደው።

እትዬ በለጡ ቁኑን ሙሉ ከልጁ አጠገብ አልጠፉም፤ ከሰዓት በኋላ አይተውት የማያውቁት ዓይነት ብርሃን ወደ ቤት ገባ። ከየት እንደመጣ ለመመልከት ወደ ውጭ ወጡ፤ ከኮረብቶቹ በላይ ሐምራዊ ቀለም ያለው ደመና እየተሰበሰበ ነው። ከታች ባለው ሸለቆ ግን ፀሐይ እስከ አድማስ ድረስ ወጥታለች። በሚያካፋው ዝናብ አሻግረው ሲመለከቷት ጨረሮቿ ብርማ ቀለም ይይዛሉ። በፀሐይዋና በደመናው መካከል ደግሞ ቀስተ ደመና ወደ ባሕር ሲጓዝ ከዋክብት በሰማይ ላይ መንቦግቦግ ጀመሩ።

ልጁ ከለበሰው ብርድ ልብስ ሌላ ምንም አልነበረም። ለመኝታም ቢሆን ያለው ምንጣፍ እንግዳው ልጅ የተኛባት ነች። እትዬ በለጡ ግን ዛሬ መተኛት አልፈለጉም፤ እሳቱ እያለቀ ያለውን ከሰል ተጠግተው ቁጭ ብለዋል። አንዳንዴ ቢያንቀላፉም

በአብዛኛው ግን ቀን የሠሩትን ያሰላስላሉ። የልጁ ሌባ ወይም ወንበዴ መሆን ከዚህ በኋላ አያሳስባቸውም። እጆቹም በመላው ዓለም ካሉ ልጆች እጅ ጋር ተመሳሳይ ነው። በእነዚያ ትናንሽ እጆቹ ይዞ በዓይኖቹም እየለመናቸው «ከእኔ ጋር ሁኑ ጥለውኝ አይሂዱ» ብሏቸዋል። እነዚህን ቃላት ራሳቸው ደገሟቸው። ከዚያም «ግን ለማን ነው የተናገርኩት? ለልጁ ነው ወይስ ለኢየሱስ? በስሙ ልጁን ተቀብያለሁና» አሉ። ከዚህ የበለጠ ማሰብ አልቻሉምና ደከማቸው።

ከፍሏ በጨረቃ ብርሃን ደምቃለች፤ አትዬ በለጡ ዘወር ብለው ልጁን አዩት። ሰውነቱ በላብ ርሷል። ትኩሳቱ እንደለቀቀው ገመቱ፤ ከእንቅልፉ ሲነቃ የት እንዳለ እስኪያውቅ ግራ ገባው። የፎጣ ቁራጭ አምጥተው ላቡን ሲያደርቁለት ጥርሱ ይንገጫገጭ ነበር። ከዚያም እሳት አነደዱ፤ የተረፈውን ቡና አፍልተው ሰጡት። እርሳቸውን ተደግፎ ከጠጣ በኋላ እጃቸውን ሳማቸው፤ ከዚያም ዐይኖቹን ጨፈነ፤ አጎንብሰው ሲመለከቱት ቆዩ። አሁን ትኩሳቱ እንደ ወጣለት ተረድተዋል፤ በመጨረሻም በሰላም ተኛ። እንደገና ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰደው።

ከፍሏ በሰላም የተሞላች መሰለች። አትዬ በለጡ እንደዚህ ቀን ደስ ብሏቸው አያውቅም። እንደሌላው ጊዜ ዛሬ ፍርሃትና ጭንቀት የለባቸውም፤ በጀርባቸው ጋለል ብለው ዐይኖቻቸውን ጨፈኑ። እርሳቸውም እንደ ልጁ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰዳቸው። ዛሬ መሬቱ አልቆረቆራቸውም፤ ብርዱም አልተሰማቸውም።

በመጨረሻ ከእንቅልፋቸው የነቁት የባልዲ ኳኳታ ሰምተው ነው። ልጁ በሩ አጠገብ ተቀምጦ ፀሐይ ይሞቃል። ፊቱ የገረጣና አሁንም የሚያስለው ቢሆንም እንኳ እንደተሻለው ያስታውቃል። ከእንቅልፋቸው መንቃታቸውን ስላወቀ እንደተቀመጠ አተኩሮ ያያቸው ነበር። በጧት ተነስቶ ብዙ ሥራዎችን ሠርቷል፡- ቤቱን ጠርጓል፥ እሳት አቀጣጥሏል፥ ተጨማሪ ማገዶ አዘጋጅቷል፥ ውኃ ቀድቶ አስቀምጧል፤ ለዶሮዎቹ በማለዳ ምግባቸውን ሰጥቷል፥ አሁን ደግሞ ዛሬ የተጣሉትን እንቁላሎች ከነካርቶኑ አስረከባቸው።

ከዚያም እንዲህ አላቸው «ሁልጊዜ ጠዋት እንዲሁ አደርጋለሁ። ወደ እረኝነት ከመሄዴ በፊት የማገዶ እንጨት እለቅማለሁ፥ ማታ ማታ የአትክልት ቦታዎትን እየቆፈርኩ አለማዋለሁ፥ ውኃ እቀዳልዎታለሁ፥ ቤትዎትንም እጠርጋለሁ፥ እርስዎን ለመርዳት የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ።»


እትዬ በለጡ ዙሪያውን ተመለከቱና ባዩት ነገር ሁሉ ተገረሙ። «በዚህ ዓይነት ልቀጥል አልችልም፤ የሚረዳኝ እፈልጋለሁ» ብለው ጸልየው ነበር። አሁን ጸሎታቸው ተመለሰ።

የተናገረው ሁሉ ተቀባይነት እንዳገኘ ስላመነ ልጁ ተመልሶ ቁጭ አለ። ባይናገረውም እንኳ አንድ ያላነሣው ጥያቄ ነበር፤ እንዲህ እየረዳቸው አብሯቸው ለመኖር ይፈልጋል። እትዬ በለጡም ይህንን ስለተረዱ ልጁ ከእርሳቸው ጋር ለመኖር መፈለጉ አስደንቋቸዋል።

ለቁርስ የተዘጋጀውን ዳቦ በቢላዋ መቁረስ ጀመሩ፤ ዳቦውን ሲቆርሱ ሳለ ኢየሱስ የሚያበራ ልብሱን እንደለበሰ ብቅ የሚል መሰሏቸው ነበር። ግን በቤታቸው ያለው ያረጀና ያደፈ ልብስ የለበሰው ልጅ ነው፤ እግሮቹን አጣምሮ በወለሉ ላይ ተቀምጧል።

በእርግጥም ይህ ትንሽ እንግዳ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ ነው።

# ኩታው



# ኩታው

## ማለዳ

መልካሙ ከእንቅልፉ ነቃ። የከተማዋ መንገዶች በግራጫ ብርሃን እየደመቁ ነው። በጣም ስለበረደው አሮጌውን ኩታ ተከናነበ። ፊቱ በመጠምጠሚያ ተሸፍኗል፤ ያንን ወደ ጎን ካደረገ በኋላ ለመገላበጥ ሞከረ። በዙሪያው የሚሆነውን ለማየት ፈልጓል። ግን በሩን ከፍቶ ብርድ እንዲመታው አልፈለገም።

በቡና ቤቱ ውስጥ የተኛው መልካሙ ብቻ አልነበረም፤ ሌሎችም ልጆች አሉ። የማታው የሲጋራ ጢስ ቤቱን እንዳፈነው ነው፤ ያልታጠቡ ብርጭቆዎች በጠረጴዛው ላይ ይታያሉ። ልጆቹ መኖሪያ ቦታ አልነበራቸውም፤ ብርዱንም ስለፈሩ ዝም ብለው ተኝተዋል።

መልካሙ በሃዘኔታ ተመለከታቸው። በዚህ ስፍራ ብዙ ያልቆየ ቢሆንም ብርዱና መባነኑ ከአሁኑ አስጠልቶታል። መሬት ላይ መተኛት አይመችም። ዱሮ ግን የዚህ ልምድ ነበረው። ችግሩ መወሰኑ እንጂ ሰው አንድ ጊዜ ከተኛና እንቅልፍ ከወሰደው የመሬቱ መቆርቆር፥ ረሃቡ፥ የልብሱ መቆሸሽና ቤት የለሽነቱ ትዝ አይለውም። መልካሙ አንዳንድ ጊዜ ሕልም ያያል፤ ይኸውም በተራራው ላይ ባለው የእናቱ ቤት እንደተኛ ነው። ዛሬ ሌሊትም ያየው ሕልም ተመሳሳይ ሳይሆን አይቀርም። ገና ሙሉ በሙሉ እንቅልፉ ባይለቀውም እናቱን ያስታውሳል። ተራ የገጠር ሰው ብትሆንም እንኳ ለእርሱ ከፍተኛ ፍቅር ነበራት፤ ብዙ ጊዜ ለእርሱ የሚበላው ዳቦ

ሰጥታ ራሷ ጠሟን ታድር ነበር። ገና በወጣትነቷ የሞተችውም በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም። የእናቱን ቤትና በአጠገቡ ያሉትን ተራሮች ካየ ሦስት ዓመታት አልፈዋል። ምን እንደሚመስሉ እንኳ ትዝ አይለውም። ወቅቱ ክረምት ስለሆነ ይህን ጊዜ በበረዶ ተሸፍነው ሳይሆን አይቀርም፤ ነፋሱም ኃይለኛ ይሆናል።

በተራራማ አካባቢ መኖር ደስ ይላል፤ አካባቢው ንጹሕ አየሩም ትኩስ ነው። ከተማው ግን ይሞቃል፤ መልካሙ ይህን ሲያስብ ቆየና ብስጭት እየታየበት ወደ በሩ አመራ።

የውጪው ብርድ ስለመታው አረማመዱን ፈጣን አደረገ። ጥርሶቹ ይንገጫገጫሉ፤ ገና ከጠዋቱ 12 ሰዓት ቢሆንም እንኳ ስለራበው ቁርስ ለማግኘት ቸኩሏል። በአቅራቢያው ካለው ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ጥሪ ይሰማል፤ መልካሙ ግን ጸሎት ምን እንደሆነ አያውቅም። አሁን የሚሄድበት ቦታ ወይም የሚሠራው ሥራ የለውም። በተራራው ላይ ስለነበረው ቤት እያሰበ ሲሄድ መንገዱ አላልቅ አለው።

የሚሄደው ወደ ባሕሩ ዳርቻ ነው። እዚያ አየሩም ቀለል ይላል፤ ብዙ ትርምስ የለም። ከዚህም በላይ ሮጥ ሮጥ እያለ ብርዱን በሙቀት ሊተካ ይችላል። በግራና ቀኝ ያሉት ሱቆች ገና አልተከፈቱም። ከእነርሱ በታች የመርከቦች መጠጊያ የውኃ ውስጥ ግንብ ይገኛል። መርከቦቹ ወደ ወደቡ የመግባት ተራ እስኪደርሳቸው እዚህ መልሕቃቸውን ጥለው ይቆማሉ። ከዚያ አጠገብ የባሕሩ ዳር አሸዋ ለጥ ብሎ

ተኝቷል። ፀሐይ ብቅ ስትል በባሕሩ ላይ የምትፈጥረው ነፀብራቅ በጣም ደስ ይላል፥ መልካሙ ግን ብቸኝነት ተሰማው።

ከዚያም ከርቀት የሚያዩት ዐይኖቹ አንድን ነገር ተመለከተ። በጣም ርቆ ባለው ተቃራኒ የባሕሩ ዳርቻ አንዲት የዓሣ ማጥመጃ ጀልባ ትንሳፈፋለች። ከእርሷ የወረዱ ጥቂት ሰዎች ደግሞ ወደ ባሕሩ ጠርዝ እየሄዱ ነው። ይህ ምን ማለት እንደሆነ መልካሙ ያውቃል፤ ማታ የጣሉትን መረብ ሊሰበስቡ ነው። መልካሙ አሁን ቁርስ ለማግኘት ይችል ይሆናል። ኩታውን ከትከሻው አውርዶ ወገቡ ላይ አሰረና በአሸዋው ላይ መሮጥ ጀመረ። ባሕሩ የሚተፋው ውኃ ከፊቱ እየተጋረጠ ቢይዘውም የባዶ እግሩን ኮቴ ብቻ እየተወ ገሠገሠ።

አጠገባቸው ሲደርስ ሁኔታቸው ጥሩ አልነበረም፤ በክፍያ ባለመስማማታቸው ሁለት ልጆች አንሠራም ብለው ሄደዋል። መልካሙ በአንድ በኩል ተገቢው ጊዜ ላይ የደረሰ ይመስላል። «እኔ መረቡን ልጎትትና ዓሣዎቹን ወደ ገበያ በመሸከምም ልረዳችሁ እችላለሁ» አላቸው ከድካም የተነሳ በኃይል እየተነፈሰ።

አቀራረቡ በጣም ግልጽ ነበር። ዓሣ አጥማጁ ይህ ልጅ ሥራ እንደሚፈልግ ብዙ ዋጋም እንደማይጠይቅ ለመረዳት ጊዜ አልፈጀበትም፤ እናም ጥቂት ገንዘብ እንደሚከፍለው ነገረው፤ መልካሙ በዚህ ተናደደ።

«በጣም አነሰ!» አለ በብስጭት።

«ተወዋ፤ የሚጎትቱ ሞልተዋል!» ብሎ መለሰለት ዓሣ አጥማጁ የሸሚዙን እጅጌ እየሰበሰበ።

በእርግጥ ብዙ ልጆች ነበሩ፤ አሁንም እየሮጡ በመምጣት ላይ ናቸው። ስለዚህ መልካሙ ፈጥኖ መወሰን አለበት፤ ምርጫው አንድም በርካሽ ዋጋ መሥራት ካልሆነም ጦም ውሎ ማደር ነው። እየተበሳጨ ኩታውን በአሸዋው ላይ አስቀምጦ በጆልባዋ በኩል ሄደና መረቡን ለመጎተት ተዘጋጀ። ሌሎቹም ሰዎች በረድፍ ስለነበሩ ዓሣ አጥማጁ «አንድ፥ ሁለት፥ ሦስት» ብሎ ሲቆጥርላቸው መጎተት ጀመሩ። ሰዎች መረብን በሕብረት ሲጎትቱ ማየት ደስ ይላል። ጎልማሶች፥ ወጣቶችና ልጆች ሁሉ በአንድነት ይጨዋጨዋሃሉ። ጡንቻቸውን አጠንክረው እግራቸው በአሸዋው ውስጥ እስኪሰጥም ድረስ ይጎትታሉ፤ እናም ርቆ የነበረው መረብ ከባሕሩ ወደ መሬት ይመለሳል። ከዚያም ያለ የሌለ ኃይላቸውን አሰባስበው ይጮኹና መረቡን ከነሸክሙ መንጭቀው መሬት ያሳርፉታል። ያኔ ለመቁጠር የሚያስቸግር የዓሣ መአት በመረቡ ውስጥ ተሰግስጎ ይገኛል። ብርማው የዓሦች ቀለም በፀሐይ ሲያብረቀርቅ ማየት ደስ ይላል፤ ከዚያ በኋላ የመለየቱ ሥራ ይከናወናል፤ ከሚጠመደው ዓሣ በጣም ብዙው የማይጠቅም ዓይነት ነው። ዝልግልግ ዓሣ፥ የኮከብ ቅርጽ ያላቸውና የማይበሉት ሁሉ ይወረወራሉ። ሰርዲኖችን ጨምሮ ሌሎች ለምግብነት ሊውሉ የሚችሉ ደግሞ የውኃ መንጠባጠቢያ ቀዳዶች ባላቸው የእንጨት ሳጥኖች እየተቆለፉ

በልጆቹ ሸክም ወደ ገበያ ይወሰዳሉ። ልጆቹ ይህን ሲሠሩ በጨዋማ ውኃ መራሳቸው የተለመደ ነው።

መልካሙ ሊሠሩ ፈልገው ዕድሉን ያላገኙ ልጆች ሳይቀድሙት አንድ ሳጥን ዓሣ ለራሱ አስቀረ። ልጆቹ ግን ከአሁኑ የማጓጓዙን ሥራ በመፈለግ መጣላት ጀምረዋል። ስለዚህ ቶሎ ብሎ ከዚህ አካባቢ መሄድ እንዳለበት መልካሙ አሰበ። ከተሸከመው ሳጥን የሚፈሰው ውኃ አንገቱን እያራሰው ስለመጣ ፈጠን ብሎ መራመድ ጀመረ፤ ግን ደስ ብሎታል፥ አሁን ቁርስ ለመብላት የሚያግደው ነገር የለምና።

ወደ ገበያው የሚወስደው መንገድ ዳገታማ ስለነበር መልካሙን ደከመው፤ እጆቹም ደነዘዙ። ገበያው ግን በዚህ ሰሞን ሞቅ ያለ ነው። ክርስቲያኖች የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት መታሰቢያ የሆነውን ገና ነገ ያከብራሉ። ለዚህም ዶሮዎችን ይገዛሉ፤ ኬክና አበቦችን የሚገዙም አሉ። የሚችሉም ለልጆቻቸው አሻንጉሊት ይገዛሉ። የሚሸጡ የገና ዛፎችና የተለያይ አበቦች በየጥጉ ሞልተዋል። ገና ከጠዋቱ 2 ሰዓት ቢሆንም ገበያው ከተለያየ አካባቢ በመጡ ገበያተኞች ተጨናንቋል። ዘንቢሎቻቸውን ይዘው በዋጋ ይከራከራሉ።

መልካሙ ዓሣዎቹን ካራገፈ በኋላ ክፍያውን ተቀበለ፤ በእውነቱ ክፍያው ከዚህ መብለጥ ነበረበት። ባለቤቱ ድሆችን በማታለልና በመበዝበዝ የሚኖር ሰው ነው። መልካሙም ከዚሁ አላመለጠም። ለነገሩ የተሰጠው ገንዘብ ቢያንስ ቁርሱን ይገዛለታል። አራት ትናንሽ ዳቦዎች ከአንድ ብርጭቆ ሻይ ጋር ይበላል። ከዚያ ደግሞ ገበያው አካባቢ ዘወር ዘወር እያለ ከገና

ገበያ የምትመለስ የቤት እመቤት ይፈልጋል፤ ከተስማማች ዘንቢሏን ይሸከማል።

ቀኑ በፀሐይ እየደመቀ አየሩም በጥቂቱ እየሞቀ ነው። ከክረምት ፀሐይ በቂ ሙቀት አይገኝም። መልካሙ ኩታውን አስታወሰ፤ ግን የት እንደጣለው ጠፋው።

አፍታም ሳይቆይ ግን በባሕሩ ዳር አሸዋ ላይ እንዳስቀመጠው ትዝ አለው። ወደ ገበያው ለመምጣት ቸኩሎ ነበር። በዚህ ላይ መረብ መጎተቱና መሸከሙ ሰውነቱን ስላሞቀው ልብስ አላስፈለገውም።

ረሃቡ ተረሳው። ኩታው ከጠፋ የሚያጋጥመው ችግር በቀላሉ የሚገመት አይሆንም፤ ከገበያው ወጣና በፍጥነት እየተራመደ ቁልቁለቱን ወረደ። ወደ ባሕሩ ዳርቻ እየሮጠ ደረሰ፤ ውኃው ወደ ምድር መምጣት ስለጀመረ አካባቢውን ሸፍኗል። መልካሙ ውኃው ወገቡ ጋ እስኪደርስ ድረስ ወደ መሃል ገባ። አሳቡ ኩታው ላይ ስለነበረ የውኃው ቅዝቃዜ አልተሰማውም። ዙሪያውን በጉጉት ተመለከተ፤ ቦታውንም አገኘው። ጀልባዋ በቦታዋ ቆማለች። አይፈለግም ተብሎ የተጣለው ዓሣም እዚያው ተከምሯል፤ ኩታው ግን የለም።

ከዚህ በኋላ ኩታውን መፈለግ ትርፉ ድካም ነው። ሌላ ልብስ ማግኘት አስቸጋሪ ስለሆነ ሁኔታው አሳዛኝ ሆነበት። ብርዱ ደግሞ እየጨመረ ሄዷል፤ እንግዲህ ቢያንስ አቡጀዲ ጨርቅ ለመግዛት ገንዘብ ማጠራቀም አለበት። ቁርሱን ሁለት ትናንሽ ደረቅ

ዳቦዎችን ለመብላት ወሰነ። የሻይና የቀሩትን ሁለት ዳቦዎች ሂሳብ ማስቀመጥ አለበት።

መልካሙ በምሬትና በንዴት ወደ ከተማ ተመለሰ፤ ፀሐይ ሙሉ በሙሉ ወጥታለች። ወገግታውና አየሩ ጥሩ ነበር፤ ሰዎች ግን ከፉዎች ናቸው። ግን ለምን?

ዓሣ አጥማጁ ሊከፍለው ከተስማማው ገንዘብ ግማሹን ሰጠው። በዚህ ላይ ኩታው ተሰረቀ። መልካሙ ኑሮው በጣም አስጠላው።

*እኩለ ቀን*

አንዲት አነስተኛ መርከብ ልክ ከቀኑ 5 ሰዓት ላይ ወደ ባሕሩ ዳርቻ መጣች። አሁን ለመርከቦቹ መጠጊያ በተሠራው የውኃ ውስጥ ግንብ አካባቢ ናት። መልካሙ በፍጥነት ወደዚያው አመራ። በየቀኑ ደስ ከሚሉት ጊዜያት ዋነኛው ይሄ ነው። ለእራቱ የሚሆነውን ሥራ አሁን ያገኛል፤ ዋናው ቀድሞ መገኘቱ ነው፥ ያለበለዚያ ችግር አለ። መርከቧ አንድ ናት፤ ሥራ ፈላጊዎቹ የጎዳና ልጆች ግን በርካታ ናቸው። ለሁሉም የሚበቃ ሥራ የለም።

መርከቢቱ ኃይለኛ የጥሩንባ ድምፅ ካሰማች በኋላ መልሕቅ ጣለች፤ መንገደኞችና ነጋዴዎች ሻንጣቸውን እየያዙ የፍተሻ ቦታውን ሲያልፉ ልጆቹ በንቃት ይከታተሏቸዋል። ከዚያም ወደ እነርሱ ጠጋ ብለው «ሻንጣ እንያዝ? ከተማችንን እናስጎብኛችሁ? ጥሩ ሆቴል እናሳያችሁ?» በማለት ይጠይቃሉ። ለአገልግሎታቸው የሚቀበሉት ገንዘብ ብዙ አይደለም፤ ቢያንስ ቢያንስ ግን የሚሸከሙት ሻንጣ አያጡም።

መልካሙ ከጎብኚዎች ጋር ብዙም አይቀራረብም። በጣም ከሲታና በዓይኖቹም ኃዘን የሚነበብበት ነው። ቱሪስቶቹ እዚህ የመጡት ስለ ድህነትና ረሃብ ለማሰብ አይደለም፤ ደስታን ፍለጋ ስለሚጓዙ ጥሩና ንጹሕ ልብስ የለበሱ አስገራሚና በራስ የመተማመን መንፈስ ያላቸውን ልጆች ማስከተል ይወዳሉ። በተራራማው አካባቢ በብቸኝነት መኖር የለመደው መልካሙ የዚህን ግርግር ሕይወት መልመድ አልቻለም፥ ግን አንዳንድ ጊዜ ይቀናዋል። ዛሬም አንዲት ወጣት ሴት አጋጠመችው። አጭር ቀሚስ ለብሳ ካሜራና ከሩቅ የሚያሳይ መነጽር አንግታለች። ብቻዋን ስለመጣች ርዳታ እንደምትፈልግ ግልጽ ነው። የሚያውቃቸውን ሦስት የእንግሊዝኛ ቃላት ተጠቅሞ «ሁሉንም እኔ አሳይሻለሁ» አላት። በተቻለው መጠን ዘመናዊ ወጣት ለመምሰል እየሞከረ አስር ብር ብቻ እንድትከፍለው ጠየቃት።

ልጅቷ ለመወሰን ተቸገረች፤ ነገር ግን አንድ ሲጋራ የሚያጨስ ወፍራም ሰው ድንገት አጠገባቸው ደረሰ። ማንም ሳይጠይቀውም ጥልቅ ብሎ እንዲህ አላት፤ «ከሁለት ብር በላይ መክፈል የለብሽም። እኔ አንቺን ብሆን አስተማማኝ የሆነ አስጎብኚ እፈልግ ነበር፤ እነዚህ ልጆች ሌቦችና አጭበርባሪዎች ናቸው።»

ጎብኚዋ መልካሙን በክፉ ዓይን ካየችው በኋላ ጥላው ዘወር አለች። መልካሙ ባለፀጉር ካፖርት የለበሰውን ወፍራም ሰው ጠላው። እርሱ እንደሆነ ርቦት አያውቅም። ያንንም ተናግሮ ልጅቷን ይዞአት ሄደ። ምናልባትም እጅግ ውድ ዋጋ ወደሚያስከፍል ሆቴል ይወስዳታል። በዚያ አብሯት ይበላል፥

ይጠጣል፥ በመጨረሻም ያጨሳል። ያም ሆነ ይህ አሁን ጊዜ ማባከን አይጠቅምም፤ ያለፈው አልፎአል።

አሁንም ፈጠን ብሎ ሌላ ሥራ መፈለግ አለበት፤ ያለበለዚያ ባዶ እጁን መቅረቱ ነው። በሩቁ አንዲት ሴት አየ። ልጅ ታቅፋለች፥ ትልቅ ሻንጣም ይዛለች። ለታክሲ ለመክፈል አቅም ያላት አትመስልም፤ የሚችለውን ማድረግ አለበት። በቀጥታ ወደ እርሷ ሄዶ «ልሸከም?» ሲል ጠየቃት፤ ሻንጣውን ሰጠችው፤ ተሸክሞም መራመድ ጀመረ።

ገና አስር ሜትር ያህል እንደ ሄደ አንድ ሰው ደርሶ የደከመችውን ሴት አገላብጦ ሳማት፤ ልጇንም ከእርስዋ ተቀብሎ አቀፈው። ከዚያ ሻንጣውን ተቀብሎ ተሸከመና ለመልካሙ ሃያ ሳንቲም ወረወረለት። ሊከራከር አልፈለገም። የዕለቱ ጠቃሚ ጊዜ እንዲሁ ባከነ፤ የተገኘው ሃያ ሳንቲም ብቻ ነበር።

መልካሙ ማዕበሉን እያየና ነገሮችን በጥንቃቄ እየተመለከተ በባሕሩ ዳርቻ መራመድ ጀመረ። እኩለ ቀን ሆኗል፥ ወደ ገበያው ለመመለስ ግን አልፈለገም። ከግርግሩ ርቆ ጥቂት ጊዜ ብቻውን ለመሆን ወሰነ። በዚህ መንደር ውስጥ በባሕሩ ዳርቻ ካልሆነ በቀር ጸጥተኛ ስፍራ ማግኘት አይቻልም። መልካሙ አንዳንዴ ጸጥ ባለ ስፍራ መቆየትን ይወዳል፤ ከተማ ማለት ሁሉ ለራሱ ብቻ የሚኖርበት ብልጥና ጉልበተኛ የሆኑ ሀብት የሚያገኙበት ቦታ ነው። ወደ ተራራማው መንደሩ መመለስ እንዲሁም ድንጋይና ወንዞቹን ማየት ናፈቀው፥ ግን እናትና አባቱ

ሞተዋል። መኖሪያ ቤትም አያገኝም። እዚህም ቢሆን ቤት የለውም። በባሕሩ ላይ አፍጥጦ ለረዥም ጊዜ አሰበ።

ጠዋት መረቡን ወደ ጎተቱበት ቦታ ተንቀሳቀሰ። ጀልባዋ አሁንም ከስፍራዋ አልተነቃነቀችም። አንድ ፀጉሩን የተላጨ ልጅ ግን እግሩን አጣምሮ ተቀምጦ መረብ ይጠግናል። መልካሙን እንዳየው ለረዥም ጊዜ በጥንቃቄ አስተዋለው።

«ጠዋት መረብ ስትጎትት ነበር አይደለም?» አለ መላጣው።

«አዎን» ሲል መለሰ መልካሙ ብዙም ስይደነቅ።

«አይቼሃለሁ፤ ኩታህ ጠፍቶብሃል አይደል?»

«አዎን የት አለ?» ሲል ጠየቀ መልካሙ በጉጉት።

መላጣው ልጅ ድቡልቡል ድንጋይ ወደ ሰማይ እየወረወረ መቅለብ ጀመረ፤ ለተወሰነ ጊዜ ጸጥታ ሰፈነ።

«ብነግርህ ምን ትሰጠኛለህ?» አለ መላጣው በድንገት።

«የምሰጥህ ነገር የለኝም፤ ዓሣ አጥማጁ በክፍያ አታለለኝ። አሁን ንገረኝና ሌላ ጊዜ እከፍልሃለሁ» አለ መልካሙ እንባ እየወረደው።

የኩታው አስፈላጊነት ተሰምቶታል።

መላጣው ልጅ ራሱን ነቀነቀ፥ ማንም ማንንም ሊያምን አልቻለም።

«አስር ሳንቲም ክፈል፤ ከዚያ ቤቱን አሳይሃለሁ፤ ኩታህን የሰረቀው ሰው በጀልባ ስለሄደ በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት አታገኘውም፤ ሰውየው ጎረቤቴ ነው፤ ወደ ቤቱ ሲወስደው አይቻለሁ፤ ቤቱ ያለችው አንዲት ሴት ብቻ ናትና ዕቃህን ልትወስድ ትችላለህ» ካለው በኋላ ቀና ብሎ ሳይመለከተው መረቡን መጠገን ቀጠለ።

መልካሙ አስር ሳንቲሙን እግሩ ሥር ሲወረውርለት ግን አንስቶ ያዘና ቆመ።

«ና ተከተለኝ» አለ መረቡን እየጠቀለለ።

ከባሕሩ ዳርቻ ተነስተው የባቡሩን ሐዲድ በመሻገር በጨው ማምረቻው ሜዳ ላይ ገሠገሡ። በበጋ ጊዜ ውኃ ከባሕሩ በቦይ እየተጠለፈ በሜዳው ላይ እንዲንሳፈፍ ይደረጋል። ፀሐይ ውኃውን ካተነነው በኋላ ጨው ከሜዳው ላይ ይታፈሳል፤ በክረምት ግን ሥራው ስለሚቋረጥ ጭር ይላል።

«ያውልህ ቤቱ» አለ መላጣው ልጅ።

«ደህና ሁን፤ እግዚአብሔር ይርዳህ» አለ ደገመና።

ልጁ ወደ ራሱ ቤት ከገባ በኋላ መልካሙ ቆም ብሎ አሰበ። መጀመሪያ ፈራ፥ ቆይቶ ግን ብስጭቱ ድፍረት ሰጠውና ወደ በሩ ተጠግቶ በኃይል አንኳኳ፤ ከዚያም ኮስተር ብሎ ጠበቀ።

መጀመሪያ መልስ አልነበረም፥ ቆይቶ ግን አንድ የደከመ ድምፅ «ይግቡ» አለ።

መልካሙ ሲገባ ቤቱ ባዶ ከመሆኑም በላይ ጨለምለም ብሏል፤ በአንዱ ጥግ የዓሣ ማጥመጃ

መረብ የተከመረ ሲሆን የአህያ ውርንጭላም ታሥሯል። በሌላው ጥግ ደግሞ አንዲት ወጣት ሴት በሰሌን ምንጣፍ ላይ ተቀምጣለች። በእጇ የያዘችው ገል እሳቱ አልቆ አመዱ የቀረ ሲሆን አልፎ አልፎ ታቃስታለች። ከአጠገቧ አንድ የጎረቤት አሮጊት ሴት ተቀምጠዋል። በእግራቸው ሥር በመልካሙ ኩታ የተሸፈነች ትንሽ ሕፃን ትገላበጣለች።

አሃ! ለካስ መላጣው ልጅ እውነቱን ነው፤ ይህ ቤት የሌቦች ጎሬ መሆን አለበት፤ ዛሬ ግን ተይዘዋል አለ በልቡ። ኩታውን ከተቀበለ በኋላ ፖሊስ ጠርቶ ጥፋታቸውን እስኪያምኑ ድረስ እንዲቀጡ ማድረግ ይችላል። ሆኖም መልካሙ እድሜውን ሙሉ አንድ ቀን እንኳ ከፖሊስ ጋር የሚያገናኘው ጉዳይ አጋጥሞት አያውቅም፤ ሆኖም ለሰዎቹ ይህን ማስታወሱ አይከፋም።

«ኩታዬን የሰረቀው ሰውዬ የት አለ?» ብሎ ጠየቃቸው በጩኸት፤ «በአስቸኳይ ብትመልሱልኝ ይሻላል፤ ያለበለዚያ በግማሽ ሰዓት ውስጥ ፖሊስ ይዤ እመጣለሁ። ሰምታችሁኛል?»

ወጣቷ ሴት በብዙ ችግር ዘወር ብላ አየችው። ሌላ ነገር የምታስብ ስለምትመስል ሙሉ በሙሉ እንዳልሰማችው መልካሙ ተረዳ፤ ስለዚህም ጩኸቱ ዋጋ ቢስ ሆነበት። የደከመችው እናትና የታመመችው ሕፃን እርሱን የሚከራከሩበት አቅም የላቸውም። ከጎረቤት የመጡት ሴትዮ ደግሞ ነገሩ አይመለከተኝም ለማለት አፍጥጠው አዩት። በጩኸቱ

የደነገጠ ፍጡር ቢኖር ጥግ ላይ የታሠረችው የአህያ ውርንጭላ ብቻ ነበረች፤ ወደ ኋላዋ አፈገፈገች።

«ውሰደው!» አለች ወጣቷ ሴት ወደ ኩታው እያመለከተች፥ «ባሌ በጀልባ ርቆ ሄዷል፤ እስከ ነገ ምሽት አይመለስም።»

ከዚያም ፊቷን ወደ ግድግዳው አዙራ ዐይኖቿን ጨፈነች። መልካሙ ኩታውን ይዞ ከመውጣት ሌላ አማራጭ አልነበረውም፥ ስለዚህ ከምታለቅሰውና ከምትንቀጠቀጠው ሕፃን ላይ ገፈፈው፥ ልጅቷ በጠና መታመሟን ያየው ይሄኔ ነበር። አሮጊቷ ሴትዮ ሕፃኗን በቀስታ አነሡና በእናቷ ጎን አደረጓት፤ በለበሰችውም ኮት ሥር አስተኟት።

ከዚያ በኋላ የተናገረው ሰው አልነበረም። ኩታውን ትከሻው ላይ ጣል አድርጎ ከጎጆዋ ሲወጣ መጨለም ጀምሯል። ገና ከአሁኑም ብርድ አለ። ወደ ባሕሩ ዳርቻ ሲመለስ መልካሙ በረሃብ ብዛት ተዝለፍልፎ ሊወድቅ ምንም አልቀረውም። ዛሬ የተወሰደበትን ኩታ በማስመለስ ታላቅ ድል አግኝቷል። ግን ደስ አላለውም፥ ይልቅ ኀዘንና ጉስቁልና ተሰማው፤ ለምን እንደሆነ አልገባውም።

*ከሰዓት በኋላ*

መልካሙ ዳቦና ሁለት የተጠበሱ የሰርዲን ዓሣዎችን ከገዛ በኋላ ጓደኛ ፈለገ። ብቻውን መሆን አስጠልቶታል። በተለይም ያንን ጸጥ ያለ ቤት፥ የዓሣ ማጥመጃ (መረብ) ክምር፥ ፊቷ የነጣውን ሴትና የታመመችውን ሕፃን የሚያስረሳው ይፈልጋል። በአውቶቡስ ማቆሚያ ከተሰበሰቡ የጎዳና ተዳዳሪ

ልጆች ጋር ተቀላቀለ፤ እዚያም ቁጭ ብሎ ምሳውን ይበላ ጀመር።

ሁሉም ሰው ለገና በዓል ሲል ጫማውን ያስጠርግ ስለነበር ሊስትሮዎቹ ደህና ገንዘብ አግኝተዋል። በዚህ አጋጣሚ ሁሉም ወደ ገበያው ወጥተው ያዩትን ያወራሉ። በተለይ ያስገረማቸው በየሱቁ የሚሸጥ የምግብ ሸቀጥ መብዛቱ ሲሆን፥ ሌላው ገገርዎች ለዋጋ ብዙም ያለመከራከራቸው ነው።

«ክርስቲያኖች በዓሉን የሚያከብሩት እንዴት ነው?» ሲል አንድ ረዘም ያለ ልጅ ጠየቀ።

«ዶሮ፥ በግና ፍየል ያርዳሉ» ሲል መለሰ ግድግዳውን ተደግፎ የቆመ ሌላ ልጅ፤

«ከእነርሱ አንደኛው ቤት ተቀጥሬ እሠራ ነበር። ለልጆቻቸው የተለያየ ስጦታ ያዘጋጃሉ። ሲበሉ ነው የሚውሉት፥ ለእኔ ግን ምንም አይሰጡኝም ነበር።»

ከዚያም ምሬቱን ለመግለጽ ዘወር ብሎ ምራቁን ተፋ።

«ግን በዓሉን የሚያከብሩት ለምንድን ነው?» ሲል ረዥሙ ልጅ በድጋሚ ጠየቀ፤ የበለጠ ለማወቅ የጓጓ ይመስላል።

«ጌታ ኢየሱስ የተወለደበት ቀን ነው» ይላሉ በማለት መለሰ፤ ሌላው ልጅ «ደግሞ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ይላሉ።»

«እኔም ይህን አውቃለሁ» አለ ሌላው ልጅ በማስከተል፤ «ለአራት ቀናት በክርስቲያኖች ሆስፒታል ውስጥ ተኝቼ ነበር። ማታ ማታ

ሊሰብኩን ይሞክራሉ፤ ደጋግመው የሚሉት አንድ ነገር ነው። እግዚአብሔር ዓለምን እጅግ ከመውደዱ የተነሳ አንድ ልጁን ለዓለም ኃጢአት እንዲሞት ፈቅዷል።»

ከዚያም ልጁ ከሆስፒታሉ ውጭ ተጋብዞ የመጣውን ሰባኪ ንግግርና እንቅስቃሴ እያስታወሰ ያንኑ ለመድገም ሞከረ፤ በዚህም ጓደኞቹ ሳቅ በሳቅ ሆኑ።

«አንዳንዶች ይሰሟቸውና ቃላቱንም ይደግሙ ነበር፤ ግን የተሻለ ሕክምና ለማግኘት ብለው መሰለኝ» ካለ በኋላ፥ «የሆነው ሆኖ ሐኪሙ ርኅሩኅ ሰው መሆኑን አልረሳም። ብንሰማም ባንሰማም ሁላችንንም እኩል ያክመን ነበር። ለሀብታሞች አያደላም።»

ወሬያቸው ወደ ሌሎች ነገሮች ተሻገረ። ሊስትሮዎቹ ወደ ገበያው ስፍራ ተመለሱ። መልካሙና ሌሎች ጥቂት ልጆች ግን እዚያው ቆዩ። አገር አቋራጭ አውቶቡስ ሊመጣ ስለሚችል ቢያንስ ለሁለት ሰው የሚበቃ ሥራ አይጠፉም።

የከሰዓት በኋላው ጊዜ ፈጥኖ እያለቀ ነው፤ በመሃሉ ክርስቲያኖች ቤት ይሠራ እንደነበር የተናገረው ልጅ ኪሱን ፈተሸ። ወዲያውኑ የድንጋጤ ድምፅ አሰማ። «ገንዘቤ ተወሰደብኝ» ማለቱ ነበር። ከዚያም ዘወር ብሎ አጠገቡ ማን እንዳለ አየ። መልካሙ ነበር፤ ልጆቹ ተባብረው ያዙትና ፈተሹት፥ ግን ምንም አልተገኘበትም።

ኪሱ ባዶ ነው፤ ልጆቹ እርሱን ትተው ሊስትሮዎቹን ለመጠየቅና ፖሊስ ለመፈለግ ሄዱ።

መልካሙ ከዚህ ሁሉ መንገላታትና መከራ በኋላ ከዚህ አካባቢ ርቆ ለመሄድ ወሰነ። ወደ ብቸኛው ሰላማዊ ስፍራ ማለትም ወደ ባሕሩ ዳርቻ ተጓዘ። እዚያም ደርሶ ቀስ እያለ መራመዱን ቀጠለ። ለረዥም ጊዜ ቀና ብሎ አላየም፤ መሬት መሬቱን እያየ ይጓዛል። ምን ዓይነት አስቸጋሪ ቀን ነው! ሁሉም ቀኖች እንደዚህ አይደሉም፤ ጥሩ ፀሐይ የሚወጣበት፥ ሳቅና ጨዋታ የሞላበት ለምግብና ማደሪያ የሚሆን ሳንቲም የሚገኝበት ቀን ሞልቷል። ግን እኮ የሳቅና ጨዋታው መንስኤ ትክክለኛ አይደለም። የሚስቁት አንድ ሰው ወድቆ ሲጎዳ፥ ሲታለል ወይም ሲዘረፍ ዓይተው ነው። ስለሆነም ሕይወታቸውን የከበበው ስስት፥ ጥላቻ፥ ፍርሃት፥ ጠብና ርኩሰት ሁሉ አስጠላው። ከድካምና መሰልቸት ብዛት በአሸዋው ላይ ተቀመጠና በባሕሩ ላይ አፈጠጠ።

ቆይቶ ቀና አለ፤ የሰማዩን ነፀብራቅ በውኃው ውስጥ ያየው ነበር። ብርሃን ሲያርፍባቸው የሚያበሩ ክንፎች ያሉት አሞራ በአጠገቡ አለፈ። «ግን ይህን የመሰለ የተዋበ ዓለም ለምን ያበላሹታል? ከዚህ ዓይነት አስከፊ ሕይወት ማምለጥ ይቻል ይሆን?» አለ መልካሙ በአሳቡ። መልስ አላገኘለትም። እንዲህ ዓይነት ነገር ከዚህ በፊት አስቦ አያውቅም።

ከዚያም በድንገት የአውቶቡስ ማቆሚያው ንግግር ታወሰው፤ በተለይም «እግዚአብሔር ዓለምን እጅግ

ከመውደዱ የተነሳ ---» የሚሉት ቃላት በግልጥ ትዝ አሉት።

ፍቅር --- ስጦታ --- ሰላም። እንዚህ ሦስት ቃላት ሰው በሌለበት ስፍራ እንደ ተተከሉ ማስታወቂያዎች ነበሩ። ሆኖም ለመልካሙና ጓደኞቹ ትርጉም የለሽ ናቸው። የእነርሱ መለያ ጥላቻ--- ንጥቅያ ---ጥል የሚሉት ሌሎች ሦስት ቃላት ናቸው። እነዚህ ደግሞ በምንም ዓይነት ወደ ሰላም ሊመሩ አይችሉም።

ይሁን እንጂ መልካሙ የመጀመሪያዎቹን ሦስት ቃላት ዱሮ ያውቃቸው ነበር። እናቱ በጣም ትወደው ስለነበር ፍቅር አሳይታዋለች። ያላትን ሁሉ ትሰጠው ነበር። በዚህ ስጦታን አውቋል፤ በሞተችበትም ምሽት በሰላም ነበር ያንቀላፋችው። ሰላምን በዚህ ተመልክቷል። በዚያ በረዶአማ ምሽት በቤት ውስጥ የነበራትን ብቸኛ ኩታ ለመልካሙ አልብሳው ነበር።

ሰላም የት ነው ያለችው? በበጋ ወቅት ተራሮች ላይ ወይም ፀሐይ ስትጠልቅ በባሕሩ ዳር ትገኛለች? ፍቅርና ስጦታስ? የታመመችውን ረዳት የለሽ ሴት ማስደንገጡንና የታመመችውን ሕፃን መግፈፉን መልካሙ አስታወሰ፤ የእርሱ ሰላም የት እንደ ቀረ የገባው አሁን ነው። ፊቱን ወደዚያ መንደር አዞረ።

በሕልሙ እየመሰለው ተነሳና ወደ ዓሣ አጥማጁ ሰው ቤት ተጓዘ። በሩ አልተቀረቀረም። ከጎረቤት ያሉት አሮጊት ወደ ቤታቸው ስለሄዱና በኋላ ሲመለሱ የሚከፍትላቸው ስለሌለ መለስ አድርገው

ትተውታል። መልካሙ በሩን ሳያንኳኳ ቀስ ብሎ ከፈተውና ወደ ውስጥ ገባ።

ከሚበራው ኩራዝ በስተቀር የሚታይ፥ ከታመመችው ሕፃን ማቃሰት በስተቀር የሚሰማ ነገር አልነበረም። መልካሙ ግን በፊት ካየው የተለወጠ አንድ ነገር ተመለከተ። ወጣቷ ሴት ወደ ጎን ዞራና ትራስ ተደግፋ ጨቅላውን ሕፃን ታቅፋዋለች፤ ደግሞ ታጠባዋለች። ፊቷ ሰላም ሰፍኖበታል፥ ፍቅርን እያካፈለችና ያላትንም እየሰጠች ነውና።

የወለደችው መልካሙ መጥቶ ከሄደ በኋላ መሆን አለበት። ቤቱ ተጠርጎ ንጹሕ ሆኗል። ውርንጭላዋ ወደ ግድግዳው የበለጠ ጠጋ ብላ የታሠረች ሲሆን በሽተኛዋ ሕፃንም በጥጥ ጨርቅ ተጠቅልላ ማቃሰቷን ቀጥላለች፤ ሴትዮዋ ድንገት ቀና ስትል መልካሙ አንገቱን ደፍቶ በሩ አጠገብ መቆሙን አየች። በፍርሃት ከጮኸች በኋላ ጎረቤቷን ለመጥራት ግድግዳውን መደብደብ ጀመረች፤ መልካሙ ግን ፈጥኖ ተጠጋት።

«አትፍሪ» አለ መልካሙ፥ «የመጣሁት ለክፉ ነገር አይደለም፤ ለዛሬ ምሽት ኩታዬን ላበድራችሁ ነው፤ ምክንያቱም ልጅሽ ታማለች። ነገ መጥቼ እወስደዋለሁ። ነገር ግን አቡጀዲ ጨርቅ ላመጣላችሁ እሞክራለሁ፤ ለዛሬ ግን ይህንን ትልበስ።»

ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ ኩታውን አንስቶ ለልጅቱ አለበሳት። ሴትየዋ በጥርጣሬ ትመለከተው ነበር። ቅድም የመጣ ጊዜ ደረቱን ነፋ አድርጎ ሲናገር፥ ሲጮኽና ሲንጎራደድ ትልቅ ሰው ይመስል ነበር።

አሁን ግን ትሑት ሆኖና ቁጭ ብሎ ስታየው ወጣት ልጅ እንደሆነ ተረዳች፥ 14 ዓመት ቢሆነው ነው።

«ተቀመጥ» አለች ሴትየዋ በደከመ ድምፅ፤ «የሻይ ጀበናው ተጥዷል፤ አንድ ብርጭቆ ጠጣና ሂድ።»

መልካሙ እየጠፋ ወዳለው ከሰል ተጠጋና ያልበረደ የሚጣፍጥ ቅመም የገባበት አንድ ብርጭቆ ሻይ ጠጣ። ሻይ ከቀመሰ ብዙ ቀናት አልፈው ነበር።

«ለምን ኩታውን መልሰህ አመጣኸው?» ስትል ጠየቀችው አሁንም ግራ እንደ ገባት።

መልካሙ መልስ አልሰጠም፤ ለምን እንዲህ እንዳደረገ ለራሱም አልገባውም።

«የት ነው የምትኖረው?» በማለት ሁለተኛ ጠየቀችው።

«ቤት የለኝም፥ ከተራራማው መንደሬ እዚህ ከመጣሁ ገና ሦስት ዓመቴ ነው» ሲል መለሰ መልካሙ።

«እኔም እንዳንተው የተራራማው መንደር ሰው ነኝ» አለች ሴትየዋ፥ «ከሰባት ዓመታት በፊት ባሌ ወደዚህ አመጣኝ፤ ከዚያ በኋላ አልተመለስኩም። አንተ የት ሠፈር ነበርክ?»

መልካሙ የሠፈሩን ስም ተናገረ፤ የእርሷም ሠፈር ከዚያ ብዙ አይርቅም ነበር። የሚለያቸው አንድ ተራራ ብቻ ነበር።

ለካስ በአንድ መንገድ ላይ ተመላልሰዋል፤ የወይራ ፍሬ፥ ወይንና በለስን ከአንድ ኮረብታ ላይ

ለቅመዋል። ከአንድ አካባቢ የለቀሙትን ማገዶ እንድደው ይሞቁም ነበር።

ሴትየዋ በጣም ስለደከመች ብዙ ማውራት አልቻሉም፤ መልካሙ ግን ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ናፍቆቱን በንግግር ማስታመሙ ደስ ብሎታል። ባለፉት ሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ መንደሩን የሚያውቅ ሰው ሲያገኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።

በዚያ ሠፈር ስላሳለፈው ዘመን አጫወታት፤ ከዚያም በአሳቡ ወደ መንደሩ ተጓዘ። ያ ተራራና ደስተኛ ሕይወቱ ከፍየሎች ጋር መሯሯጡና ሲመሽም ወደ እናቱ ቤት እንዴት ይመለስ እንደነበር አስታወሰ። ብዙ አወራላት፤ እርሷም ጋደም እንዳለች አዳመጠችው። የጠየቀችው ጥያቄ ቢኖር በጣም ጥቂት ነው።

እርሷ ግን እንደ መልካሙ የመንደሯ ናፍቆት አልነበራትም፥ ምክንያቱም ልጆቿ የተወለዱት በዚሁ ጎጆ ውስጥ በጨው ማምረቻው ሠፈር ነው። የእርሷ ልብ ከልጆቿ ጋር እዚሁ ተቀምጧል። ለእርሷ ትዝታዋ በእጇ ያቀፈችው አዲሱ ልጅና የታመመችው ሕፃን ናቸው።

ትንሿ ሕፃን በድንገት ጮኸች፤ እናትየዋም ልታባብላት ወደ እርሷ ፈቀቅ አለች። ከእንቅልፍዋ የነቃችው ሕፃን ውኃ ጠምቷት ነበርና እናትየዋ በብርጭቆ ውኃ ካጠጣቻት በኋላ እንደገና አለቀሰች። ይህም እናቷ እንድትታቀፋት በመፈለግ ነበር። እናትየዋ ጨቅላውን ሕፃን መሬት ካስቀመጠች በኋላ እርሷን አነሳቻት።

«ምናን ነው ያመማት?» ሲል ጠየቀ መልካሙ።

«እንጃ» አለች እናትየዋ በብዙ ድካም ሕፃኗን ወደ ፊትና ወደ ኋላ እያወዛወዘች፤ «ካመማት ሦስት ቀኗ ነው። በየቀኑ ባሌን ወደ ሆስፒታል እንዲወስዳት እጠይቀዋለሁ። እርሱ ግን ወንድ እንዲወለድለት ይፈልግ ስለነበር አይወዳትም። ስለዚህ ጊዜ የለኝም የሚል ምክንያት ይሰጣል። እኔ እንዳልወስዳት ታምሜአለሁ፤ እናም መሞቷ አይቀርም፥ ግን ሆስፒታል ብትሄድ ልትድን ትችላለች።»

«እዚያ ብትሄድ እንደምትድን እንዴት አወቅሽ?» በማለት መልካሙ ሌላ ጥያቄ አቀረበ።

«ከዚህ በፊት ወስጄአት ነበር፥» አለች ሴትየዋ፤ «ያኔም ልክ እንዳሁኑ ትኩሳት ነበረባት። መተንፈስና ጡት መጥባት አትችልም ነበር፤ ሐኪሙ መርፌ ሲወጋት ግን ትኩሳቱ ጠፋ። አሁንም ብትሄድ እንደዚያው ማድረጉ አይቀርም። ሐኪሙ ጥሩ ሰው ነው፤ እዚህ እንዲመጣ እንዳንጠራው ገንዘብ የለንም፤ ማን ይወስዳታል?»

«እኔ እወስዳታለሁ፤ ሆስፒታሉንም አውቀዋለሁ፤» አለ መልካሙ ትንሽ ካሰበ በኋላ።

ሴትዮዋ ትኩር ብላ ተመለከተችው፤ ሊታመን ይችል እንደሆነ እርግጠኛ አይደለችም። ይህች ያልተማረች እናት ስለ በሽታ ብዙ ዕውቀት የላትም። ልጇ እንዳትሞት በጣም ፈርታለች። በዚህ ምሽትና በአሳሳቢው ብርድ ልጇን ወደ ሕክምና መስደድ አትፈልግም፥ ግን ደግሞ በመርፌ ፈዋሽነት ታምናለች። ምናልባት ለሕፃኗ ያላት የመጨረሻ

ዕድል ይህ ሊሆን ይችላል። ደግሞም መልካሙ የመንደሯ ልጅ መሆኑ እንድታምነው ገፋፋት፤ ስለዚህ እንዲወስዳት ተስማማች።

ትንሿ ሕፃን በእናቷ እቅፍ እንቅልፍ ወስዷት ስለነበር መልካሙ ታቅፎ ሲወስዳት አልሰማችም። በኩታው ከጠቀለሏት በኋላ መልካሙ በጨው ማምረቻው ሜዳ እያቋረጠ ልጅቷን ይዞ ገሠገሠ። ጨረቃ ወጥታለች፤ በባሕሩም ላይ ብርማ ቀለም ሠርታለች። መልካሙ ረዥም መንገድ ስለሚጠብቀው የጨረቃዋን ብርሃን ሲያይ ደስ አለው። የልጅቷ አንገት በትከሻው ላይ ያረፈ ሲሆን ትኩሳቷ ሰውነቱን አሞቀው። ወደሚሄድበት ፈጥኖ ለመድረስ አቋራጭ መንገድ ተጠቀመ። ከእርሱና ከተሸከማት ሕፃን በስተቀር በአካባቢው ማንም አይታይም። አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ሕፃኗ ለመወራጨት በቀስታም ለማልቀስ ሞክራ ነበር። መልካሙም ከአባበላት በኋላ «ብቻ በዳነች» ብሎ አሰበ።

በባሕር ውስጥ ዘልቆ ወደተሠራው የመረማመጃ ድልድይ ደረሰ፤ የቀረው ወደዚያኛው መንደር ማሻገር ብቻ ነው። ለነገው በዓል ዝግጅት ማምሻውን ገበያው ይደምቃል። መልካሙ ግን ወደዚያ መሄድ አልፈለገም። በባሕሩ ዳርቻና በአሸዋው ላይ ሰላም አግኝቷል። ይህም የገና ዋዜማውን በጨረቃ የደመቀ ምሽት፥ ይቅርታና ፈውስ የሞላበት አስመስሎታል። ለምን ሰላም እንዳገኘ መልካሙ አልገባውም፥ ምክንያቱ ግን ፍቅርን እያሳየና ያለውን እየሰጠ ስለነበረ ነው።

## ምሽት

በገና ዋዜማ የምሽቱ ገበያ ደስ የሚል ነው፤ የሱቆች መስኮቶችና በመንገዱ መሃል ያሉት ዛፎች በገና ዛፍ መብራቶች ይደምቃሉ። አካባቢው ከወላጆቻቸው ጋር ለሸርሸር በወጡና ዙሪያውን በሚቃኙ ሀብታም ልጆች ይወረራል። ማየት የተሳናቸውና አካል ጉዳተኛ የሆኑ ለማኞችም በብዛት ይመጣሉ፤ ምክንያቱም ገበያተኞቹ በዚህ ቀን የተሻለ ርኅራኄ ስለሚያሳዩዋቸው ነው። የመልካሙ ጓደኞችም በሙሉ ከዚያ አይጠፉም፤ መልካሙ ከእነርሱ ሲለይ ይህ የመጀመሪያው መሆኑ ነው። አብረው ግርግሩን ያያሉ፤ ሲያመቻቸውም ይሰርቃሉ። ዛሬ ማታ ግን የተሻለ ሥራ ስላለው ጓደኞቹን ለማግኘት አላሰበም። ሰው የማይበዛበትን የመንደሩን ጥግ መንገድ መርጦ በዚያ ዞሮ ሆስፒታሉ ወደሚገኝበት ጉብታ ስፍራ ገሠገሠ።

‹ግን ሐኪሙ ገናን እያከበሩ ወይም እየጠጡ ቢሆንስ?› ሲል አሰበ መልካሙ። በረሃብ እየደከመ ከመሄዱም በላይ ልጅቱ እየከበደችው ነው። በከንቱ እንዳልደከመ ግን አመነ።

ወደ ሆስፒታሉ እና ወደ ሐኪሙ መኖሪያ ግቢ የሚያስገቡት በሮች አጠገብ ደርሶ በየትኛው በኩል ቢገባ እንደሚሻል ሲያስብ አንድ ሰው በአታክልት ቦታው አቋርጦ ሲመጣ አየ። እናም ሐኪሙ መኖራቸውን ጠየቀ።

«መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ናቸው፤ ግን ሥራ ይዘዋል።» አለ ሰውየው።

«ልጅቷ በጣም ታማለች፤ ያመጣኋትም ከሩቅ ነው፤» አለ መልካሙ በልመና ድምፅ።

«በሩን አንኳኳና ልጅቷን አሳያቸው» ሲል መከረው ሰውየው የልጅቱን ፊጣን አተነፋፈስ ካየ በኋላ።

መልካሙ ወደ ውስጥ አዘገመ፤ የቤቱ በር ቢዘጋም በመስኮቱ በኩል የመብራት ብርሃን ይታያል። የሙዚቃና የሳቅ ድምፅም ከውስጥ ይሰማል። መልካሙ ‹ላንኳኳ ወይስ ልተወው› እያለ አወላወለ። በዓሉን እያከበሩ እንደሆነ አልተጠራጠረም፤ ከዚህም በላይ ሁሉም ጠጥተው ይሆናል። ቆይቶ በርጋታ ሲያዳምጥ ግን ጫኸትና ሳቁ የልጆች እንደሆነ ገባው፤ ስለሆነም ይህች ትንሽ ልጅ ተቀባይነት ልታገኝ ትችላለች።

እናም አንኳኳ፤ ችግር ካጋጠመውም ለመሮጥ ተዘጋጅቷል፤ ሐኪሙ ራሳቸው በሩን ከፈቱለት። ፀጉራቸው የተበታተኑ ቢሆንም እንዳልጠጡ ግን ያስታውቃል። ከልጆቹ ጋር እየደነሱ ነበር፤ ደግሞ የራሳቸውን የሦስት ዓመት ልጅ ታቅፈዋል።

ሐኪሙ ለጥቂት ጊዜ መልካሙን አስተዋሉት፤ ዐይኖቻቸው የውጭውን ጨለማ ወዲያውኑ መልመድ አልቻሉም ነበር። ልጁ የተራበ ዐይኖቹም የደከሙ ናቸው። የለበሰው ካፖርት መሳይ ልብስ በአንድ ወቅት ነጭ እንደነበረ ለማመን ያስቸግራል። ደግሞ በእጆቹ በኩታ የተጠቀለለችና ጤና ያጣች ሕፃን ታቅፎአል።

«ታማለች» አለ መልካሙ እጆቹን ወደ ሐኪሙ እየዘረጋ።

ሐኪሙ የታቀፉትን ልጅ መሬት አስቀመጡት። ትንሹ ልጅ ወደ ዳንሱ ሮጠ፤ ከዚያም እጃቸውን ዘርግተው ሕፃኗን ከመልካሙ ከተቀበሉ በኋላ ወደሚሞቀው ሌላ ክፍል ይዘዋት ገቡ።

መልካሙ ይህን አጋጣሚ ከብዙ ዓመት በኋላ እንኳ ሊረሳው የሚችል አይደለም፥ ምክንያቱም የገና በዓል ትርጉም ምን እንደሆን አሳይቶታል። አባት ልጁን አኑሮ በጨለማው ምሽት እርዳታ የሚያስፈልጋትን ሕፃን ተቀበላት።

ሐኪሙ ልጅቷን በሚገባ ካዩዋት በኋላ ደረቷ ላይ የማዳመጫ መሣሪያ አስደግፈው ይሰሙ ጀመር። ከዚያም የማቃሰቷ መንስዔ የሆነውን ትኩሳቷን ለኩ። በእርግጥም ታማለች፤ ግን እናትየዋ የፈራችውን ያህል አልነበረም። ብርድ የመታት ሲሆን በመተንፈሻ አካሏም ላይ መጠነኛ ችግር አስከትሏል።

ስለዚህ ሐኪሙ ወደ ሆስፒታሉ ሊወስዷት ወሰኑ፥ መርፌ ትወጋለች። ከዚያ በኋላ ወደ ቤቷ መሄድ ትችላለች። «እስከመለስ እዚሁ ጠብቀኝ» አሉት መልካሙን።

መልካሙ ከትልቁ ክፍል የሚመጣውን ድምፅ እየሰማ ጸጥ ብሎ ተቀመጠ። «ከየት ይሆን እነዚህ ሁሉ ልጆች የመጡት?» ሲል አሰበ፤ መቼም ሁሉም የሐኪሙ ልጆች ሊሆኑ አይችሉም። ከዚህ በፊት ልጆች ሲስቁም ሆነ በደስታ ሲጮኹ ሰምቶ አያውቅም። ወዲያው አንድ ሰው ከትልቁ ክፍል

ወጣ። መልካሙ ይህን አጋጣሚ ተጠቅሞ ወደ ውስጥ ተመለከተ። ያየውም በጣም አስደነቀው። ልጆቹ በአብዛኛው የእርሱው ዓይነት ነበሩ። ልጃገረዶቹ ረዣዥም ቀሚስ ለብሰው ፀጉራቸው ላይ ሪባን አስረዋል። ወንዶቹ ደግሞ ፀጉራቸውን ተስተካክለው ሰፋፊ ሱሪዎችን ለብሰዋል። ሁሉም ኬክ እየበሉ ነበር።

ሐኪሙ የምታለቅሰውን ሕፃን ይዘው ተመለሱ። መልካሙ ጎንበስ ብሎ እጅ በመንሳት አመሰገናቸው። ከዚያም እጁን ዘርግቶ ሕፃኗን ተቀበላቸው። አሁን ቶሎ ብሎ ወደ ቤቷ ሊመልሳት ይገባል።

ሐኪሙ ግን ያልጨረሱት ነገር ነበራቸው። በየዕለቱ ድሆችን ይመለከታሉ፤ ግን እንዲህ የተጎሳቆለ ልጅ አይተው አያውቁም፤ በዚህ ላይ ደግሞ ቀኑ የገና ዋዜማ ነው።

«እንዴ ጠብቀኝ» አሉ ሐኪሙ፥ «ነገም መርፌ መወጋት ይኖርባታል፤ የት ነው ቤትዋ?»

«ጨው ማምረቻው አካባቢ ነው፤ ግን አባቷ ስለማይፈቅድ መመለስ አትችልም፤ ዛሬም ስለሌለ ነው የመጣችው» አለ መልካሙ።

«አንተስ? ወንድሟ ነህ አይደለም? ለምን አታመጣትም?»

«ወንድሟም ምኗም አይደለሁም፤ የጎዳና ተዳዳሪ ነኝ፤ አባቷ ከተመለሰ ደግሞ እንዳመጣት አይፈቅድልኝም።»

«እናቷስ ለምን አታመጣትም?» ሲሉ ጠየቁት ሐኪሙ።

«ዛሬ ነው የወለደችው፤ መምጣት አትችልም» ሲል አብራራ መልካሙ።

«ጥሩ» አሉ ሐኪሙ፥ «ራሴ እዚያ እሄዳለሁ። አንተ ቤታቸውን አሳየኝ፤ ወደ መንደሩ ሄጄ የማየው አንድ ሰው አለ። ከእርሱ ቤት እስከ ጨው ማምረቻው በመኪና ለመሄድ አይርቀኝም፤ ና እንሂድ!»

መልካሙ ፈገግ አለ። ከዚህ በፊት በግለሰብ መኪና ተሳፍሮ አያውቅምና ተደነቀ። ሊወጡ ሲሉ ሐኪሙ መልካሙን አስቆሙት።

«በጣም የበረደህ ትመስላለህ፤ ኩታ የለህም እንዴ?»

«ኩታዬ ይኸውና» አለ መልካሙ ለሕፃኗ ማልበሱን እያመለከተ።

«ብርድ ልብስ የላትም?»

«ነበራት፤ የተወለደው ሕፃን ተጠቅልሎበታል።»

«ጥሩ እንግዲያው የአንተን ኩታ እንደለበሰች ትቆይ፤ ለአንተ የሆነ ነገር ልፈልግልህ እችላለሁ።»

ሐኪሙ ሁለቱን ደረጃ በአንድ ጊዜ እየወጡ ወደ ፎቅ ሄዱ። መልካሙ እየተደነቀ ጠበቃቸው። ቀጥሎ ምን እንደሚከተል ማወቅ አይችልም። መቼም ሐኪሙ ልብስ ይሰጡኛል ብሎ አላሰበም፥ ግን ሊሰጡት ነው።

ሐኪሙ ለገና ስጦታ ወደ ሆስፒታሉ ከመጡት ልብሶች መካከል ለመልካሙ የሚሆን አንድ ወፍራም ጃኬትና አንድ ሹራብ፥ ለዓሣ አጥማጁ ልጆች ደግሞ ትናንሽ ኮቶችን መረጡ። እነርሱን ይዘው በጣም ደስ እያላቸው ወደ ምድር ቤት ወረዱ።

«እያቸው» አሉት መልካሙን «እነዚህ ይሞቁሃል»።

መልካሙ ባለማመን በጥርጣሬ ተውጦ ዝም አለ። ይህ ነገር ፈጽሞ አልገባውም። ሊሸጡለት ይሆን--- ደግሞ አይመስልም።

«ገንዘብ የለኝም» ሲል አንሾካሾከ።

«ምንም አይደል፥» አሉ ሐኪሙ፥ «ስጦታ ነው፤ በዓል ሲሆን ስጦታ መስጠት የተለመደ ነው።»

መልካሙ ለመልበስ ሲሞክር ሐኪሙ ሕፃኗን ያዙለት። ልብሶቹ የተለበሱና የተሰፉም ነበሩ። ግን ይሞቃሉ፤ መልካሙ ታላቅ ክብር ተሰማው፤ እንዲህ ዓይነት ልብሶችን አግኝቶ አያውቅም። ከዚያም ደግሞ ማልቀስ የጀመረችውን ሕፃን እንደ ነገሩ አለበሳት። «እንሂድ እንግዲህ» ብለው ሐኪሙ መውጣት ጀመሩ። በትልቁ ክፍል በኩል ሲያልፉ ልጆቹን ለመሰናበት ጎራ አሉ። ልጆቹ ፕሮግራሙን እያጠናቀቁ ነበር። ሲወጡም በእጆቻቸው ሙሉ ኦቾሎኒ፥ ከረሜላና ብስኩት ይዞ ተመለሰ።

«ይኸውልህ፤ አንተም ከግብዣው ተካፈል» አሉ ያመጡትን ለመልካሙ እየሰጡት።

መልካሙ ግራ ተጋባ፤ የሕይወት ምሥጢር ግልጽ አልሆነለትም። ብስኩት እየበላ ሰውነቱ ሞቆ በዋናው መንገድ ላይ በመኪና እየበረረ ነው። ፈጥነው ወደ ጨው ማምረቻው ሠፈር ደረሱ። እንዴት ድንቅ ነው!

በቀጥታ ወደ ዓሣ አጥማጁ ቤት ተጓዙ፤ ሕፃኗን ይዘው ወደዚህ በመምጣታቸው ሐኪሙ በጣም ደስ አላቸው፥ ምክንያቱም ቤቱ ገና የተባለው በዓል መነሻ ስፍራ የሆነችውን ቤተልሔምን

አስታወሳቸው። ጎጆዋ ከመጎሳቆሏም በላይ ውርንጭላ ስለታሠረባት በረት ትመስላለች፤ ሴትየዋ ደግሞ እንግዳውን ሕፃን ይዛ ተኝታለች።

እናትየዋ የመልካሙን መመለስ በጉጉት ትጠብቅ ነበር፥ ግን እንዲህ ፈጥኖ ይመጣል ብላ አላሰበችም። ሐኪሙን ባየች ጊዜ ጥቂት ግር አላት፥ ምክንያቱም ባሏ ካልመጣ በቀር ገንዘብ ማግኘት አትችልም። ደግሞም ገና ከመምጣቱ ዕዳ እንዳለባቸው ብትነግረው ደስ አይለውም፤ የሆነ ሆኖ ልጅቷን ከጎኗ ሲያስተኙላት ደስ አላት።

ከዚያም ሐኪሙ ለእናቲቱ የሚከተለውን ነገሯት፤ «መርፌ ወግተናታል። ሙቀት እንድታገኝ አድርጉ፤ ፈሳሽ በብዛት ስጧት፤ ነገ እኔ ራሴ እመጣለሁ። ወፍራም ልብስ አልብሰናታል፤ ለትንሹ ልጅም አምጥተናል።»

«እኔ ግን ገንዘብ የለኝም» ስትል እናትየዋ በብስጭት ተናገረች። ሐኪሞች ቤት መጥተው ሕክምና ከሰጡ እንደሚያስከፍሉ ታውቃለች።

«ምንም አይደል፥» አሉ ሐኪሙ፤ ይህን ሲናገሩ በጭቃው ወለል ላይ ተንበርክከው በብርድ ልብሱ እጥፋት መካከል አተኩረው ሚጢጢውን እንግዳ ሕፃን እያስተዋሉ ስለነበር ክፍያ የሚባል ነገር ትዝም አላላቸውም፤ በቤተልሔም ገንዘብ የከፈለ አልነበረምና።

ሐኪሙ ወደ ውጭ ሲወጡ መልካሙ ተከተላቸው። በሐኪሙ ባትሪ እየተረዱ ወደ መኪናዋ ሄዱ። በጣም ስለመሸ ሐኪሙ ወደ መንደሩ እንዲያደርሱት መልካሙ ፈለገ።

«የት ነው የምትተኛው?» አሉ ሐኪሙ ወደ ከተማ መቃረባቸውን የሚያሳየው መብራት ጋ ሲደርሱ።

መልካሙ ጥቂት ወላወለ። የት መተኛት እንዳለበት እስካሁን አልወሰነም። በዚህ ምሽት ያያቸው ነገሮች ሁሉ ተዳምረው ያንን ቡና ቤት አስጠልተውታል፤ ወደ አዲስ ዓለም ገብቶ ነበር። ሰዎች ፍቅራቸውን በመስጠት የሚገልጡበት፥ ልጆች የሚስቁና የሚጫወቱበት መንደር ውስጥ ተቀላቅሎ ነበር። አሁን ከዚያ መውጣት እንደሚኖርበት ተገነዘበ። ነገ ጠዋት ደግሞ መንጠቅና መስረቅ እንዲሁም ጥልና ክርክር ይጠብቀዋል። ባለፉት ጥቂት ሰዓታት ያያቸው ነገሮች ሁሉ ሕልም ይሆኑበታል።

«እኔ እንጃ» አለ በመጨረሻ በደከመ ድምፅ፥ «ገበያው መሃል አውርዱኝ።»

«መኝታ ልታገኝ የምትችልበት ቦታ እወስድሃለሁ። በርኅራኄ በሆስፒታሉ አጠገብ ልጆችን የምታሳድር ሴትዮ አለች» አሉ ሐኪሙ።

«ገንዘብ የለኝም።»

«ገንዘብ አታስከፍልም፤ ያን የምታደርገው ልጆቹን ለመርዳት ብቻ ነው። ብርድ ልብስም ትሰጥሃለች፤ ሄደን እንጠይቃታለን።»

ሐኪሙ መጎብኘት የነበረባቸውን ሰው ለማየት ብዙ ጊዜ አልፈጀባቸውም። ከዚያ በኋላ እርሳቸውና መልካሙ በመኪናዋ ወደ ተራራማው አካባቢ ተጓዙ። ከዚያም በውኃ ገንዳ አጠገብ በምታስገባው ጠባብ መንገድ ላይ ካለች ትንሽ ቤት አጠገብ ቆሙ። በፋኖስ ብርሃን እየታገዙ ውኃ የሚቀዱ ሴቶችና

ልጃገረዶች ይታያሉ። ሁሉም ለታዋቂው ሐኪም ሰላምታ ሰጧቸው።

ሐኪሙ በሩን አንኳኩ። የከፈተችላቸው ሕፃን የታቀፈችና ፊቷ በፈገግታ የተሞላ ሴት ነበረች። የሐኪሙን ድምፅ እንደ ሰሙ ቤተሰቡ በሙሉ ወደ በሩ መጡ። ከእነርሱ ጋር እራት እንዲበሉ ለመኗቸው፤ እርሳቸውም ወደ ውስጥ ገቡ። በምግቡ ዙሪያ ክብ ሠርተው ተቀመጡ። አባት፥ እናት፥ ትላልቅ ሴት ልጆችና አምስት የጎዳና ተዳዳሪ ልጆች ነበሩ። መልካሙ አንዳንዶቹን ያውቃቸዋል፤ ምግብና ቤት ፍለጋ ወደ ከተማ የተሰደዱ የሠፈሩ ልጆች ናቸው። ማታ ማት የት እንደሚተኙ አያውቅም ነበር። አሁን ገባው።

ቤቷ ትንሽ ናት። ዕቃዎቿም ያን ያህል ውድ አይደሉም፥ ግን ንጹሕ ነች። ልጆቹ የሚተኙት በላይኛው ክፍል ነው። ቤተሰቡ በሐኪሙ መምጣት ደስ ብሏቸዋል። መልካሙንም በፈገግታ ተቀብለውታል፤ ልጆቹ ብቻ በጥርጣሬ ተመለከቱት፤ አንድ ሰው ተጨመረ ማለት ክፍል ይጠባቸዋል ማለት ነው። እራትም ሊያንስ ይችላል።

«የገና ስጦታ አምጥቼላችኋለሁ» አሉ ሐኪሙ እጃቸውን በመልካሙ ትከሻ ላይ አኑረው፤ «እርሱም አዲስ ልጅ ነው» አሉ በመቀጠል።

«እንኳን ደህና መጣህ!» አለች እናትየዋ። ከዚያም ጠጋ ብለው ቦታ ሰጡት። አንገቱን አቀርቅሮ ተቀመጠ። ከሴቶቹ ልጆች አንዷ የራሷን ዳቦ ለሁለት ቆርሳ አንዱን ሰጠችው፤ ሾርባውን በማንኪያ

እየጨለፈ መጠጣት ጀመረ። ተራ ምግብ ነበር፥ ለመልካሙ ግን ጣፈጠው።

«የገና ዋዜማ ነው፤ ስለዚህ ጥቂት ጥቅሶችን አንብቡልን» አለች እናትየዋ ከመደርደሪያው ላይ አንድ መጽሐፍ አምጥታ ለሐኪሙ እየሰጠቻቸው። እርሳቸውም ማንበብ ጀመሩ። ልጆቹ ስለ ጠገቡና ስለ ሞቃቸው እንቅልፍ እንቅልፍ ብሏቸዋል። እናትየዋ ግን በንቃት ትከታተላለች። መልካሙም አዳመጠ። ከዚህ በፊት የዚህ ዓይነት ንባብ ሰምቶ አያውቅም፤ ሐኪሙ በበረት ስለተኙት እናትና ልጅ ሲያነቡ መልካሙ የዓሣ አጥማጁን ጎጆ አስታወሰ። ቀጥሎም ስለ እረኞቹና ስለ መላእክት ዝማሬ አነበቡ፤ መልካሙ ራሱ እረኛ ነበር።

«አዳኝ ተወልዶላችኋልና --- ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን፤ ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ።»

ከዚያም ሐኪሙ ግልጽ በሆኑ ቃላት መልእክቱን አብራሩት። እግዚአብሔር አዳኙን ኢየሱስን የሰጠው ዓለምን ስለሚወድ ነው።

«ሰላም በምድር» ማለት ሲበደሉ ይቅርታ በማድረግ የሚገኝ የልብ ሰላም ነው።

በጎ ፈቃድ የሚገኘው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ይህም ሁሉንም ሰው እንደ እግዚአብሔር ልጅና እንደ ቤተሰባቸው አባል እንዲመለከቱ ይረዳቸዋል። በጎ ፈቃድ ልባቸውንና ቤታቸውን ለሰዎች እንዲከፍቱ፥ እንዲረዱ፥ እንዲያገለግሉና እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል።

መልካሙ እግሮቹን አጣምሮ በወለሉ ላይ ተቀምጧል። ዐይኖቹ በሐኪሙ ፊት ላይ ተተክለዋል፤ የተደረገለት እርዳታ ጥቂት ቢሆንም ያ ለእርሱ ብዙ ነበር። ትንሿ ሕፃን ለምን የሕክምና ርዳታ እንዳገኘች አሁን ገባው፤ ምግብና ልብስ ያገኘው አሁንም መጠለያ የተሰጠው ለምን እንደሆነ ተረዳ።

እናትየዋ ልጆቹ ላይ ቤት እንዲወስዱትና ብርድ ልብስ እንዲሰጡት አዘዘች። ሐኪሙም በማበረታታት ትከሻውን መታ መታ አድርገው ወደ ቤታቸው ሄዱ።

ከቤቱ ውጭ ከዋክብቱ ያበራሉ፤ ምሽቱ የገና ዋዜማ ነው። በመላው ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ምሽት ይከበራል። እርሱ ለድሆች የምሥራችን ይዞ መጥቷል፤ ልባቸው የተሰበረባቸውን ጠግኗል፤ ሰዎችን ከፍርሀትና ከሃዘን ነፃ አውጥቷል።

ግን በሃዘን የተሞሉ በሺህ የሚቆጠሩ በከተማዋ ጥጋጥጎች ተኝተዋል። ሲነጋ ይነቃሉ፤ ስለ ገና የሚያውቁት ነገር የለም፤ ቢያውቁም ግድ የላቸውም።

የመልካሙ ሁኔታ ግን ተቀይሯል። የገና ታሪክ አስደናቂ እውነት እየገባው ነው። የልጅነት ልቡ በእግዚአብሔር ሰላም መሞላት ጀምራለች። ከአሁን በኋላ ብቸኝነትና ፍርሃት አያገኙትም፤ መጪው ጊዜ ብሩህና በተስፋ የተሞላ ነው. . .

* * *

# በታሪኮቹ ውስጥ ያሉና ከበድ የሚሉ ቃላት ትርጉም

| | | |
|---|---|---|
| ልዕልት | – | የልዑል ሚስት |
| ኮቴ | – | በእግር የተረገጠ ምልክት |
| አጎዛ | – | ከበጎች ቆዳ የሚሠራ ምንጣፍ |
| ማንኮራፋት | – | በእንቅልፍ ጊዜ ድምፅ ማሰማት |
| ነርስ | – | የጤና ባለሙያ |
| ግርግም | – | የከብቶች መመገቢያ |
| ጊታር | – | ክራር መሰል የሙዚቃ መሣሪያ |
| ኮረብታ | – | ከፍ ያለ መሬት |
| ጎስቋላ | – | ያጣና ያልተመቸው ሰው |
| ለግላጋ | – | ደስ የሚል ቁመና |
| ማሰላሰል | – | ደጋግሞ ማሰብ |
| ዕንቁ | – | ውድ ዋጋ ያለው ማዕድን |
| አሸንዳ | – | ከቤት ጣራ ጋር ተያይዞ የተሠራ የዝናብ መውረጃ |
| መልአክ | – | የእግዚአብሔር መልእክተኛ /መንፈስ/ |
| መቀነት | – | ከጨርቅ የሚሠራ መታጠቂያ |
| አድማስ | – | በዐይናችን የምናየው ክልል |
| መልሕቅ | – | በሰንሰለት የሚያያዝ መርከቦችን ለማቆም የሚረዳ ፍሬን |
| ቱሪስት | – | ለጉብኝት የሚዘዋወር ሰው |
| ዋዜማ | – | አንድ ቀን ሲቀረው |
| ሪባን | – | የሴቶች ፀጉር እንዳይበተን የሚታሰር ጌጥ |
| ኩታ | – | ነጠላ ጋቢ |